የህዝባዊ ድርጅቶች ዘርፍ
የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

(ማሰልጠኛ ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የህዝባዊ ድርጅቶች ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

(የሥልጠና ሞጁል)

ህዳር 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

የህዝባዊ ድርጅቶች ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

አዘጋጆች

ዶ/ር ደስታ ሙሉጌታ

ዶ/ር ሰሎሞን ግርማ

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኂላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ

© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ህዳር 2017 ዓ.ም

ማዉጫ

አጠቃላይ መግቢያ 6

የሞጁሉ አጠቃቀምና አቀራረብ 7

የማስልጠኛ ዘዴዎች 7

ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ 8

የስልጠና ሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ 8

መገምገሚያ ስልት 9

ምእራፍ አንድ 10

የሙስና ወንጀል ምንነት 10

1.1 መግቢያ 10

1.2 የሙስና ምንነት 11

1.3 የሙስና ዓይነቶች 12

1.4 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት 14

1.5 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች 17

ማጠቃለያ 25

ምእራፍ ሁለት 26

ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉ ተጋላጭነት እና በሕዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች 26

2.1 መግቢያ 26

2.2 ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉ ተጋላጭነት 27

2.3 በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች 38

ማጠቃለያ 48

ምእራፍ ሶስት 49

በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች የሚያስከትሉት ጉዳት እና መከላከያ ስልቶች. 49

3.1 መግቢያ 49

3.2 በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች የሚያስከትሉት ጉዳት 51

3.3 የሙስና መከላከያ ስልቶች 55

ማጠቃለያ 65

ማጣቀሻ.. 66

ራስን መገምገሚያ ቼክ ሊስት 68

አጠቃላይ መግቢያ

ሙስና የአንድን ማህበረሰብ ሁለንተናዊ አኗኗር የሚያቀጭጭ የልማትና ብልጽግና ቀንደኛ ጠላት እና የሀገርን ሉዓላዊነትና ክብር የሚያጎድፍ ዕዳ ነዉ፡፡ በመሆኑም ግለሰቦች፣ ተቋማት፣ መንግስታት፣ ከፍ ሲልም ህዝብ እንደ ህዝብ ሊዋጋዉ የሚገባ ወንጀል ነዉ፡፡ ይህን በመገንዘብ ሀገራት፣ እንዲሁም የተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት ሙስናን ለመዋጋት ብዙ ርቀት ሂደዋል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያም ሙስናን ለመዋጋት የተለያዩ ሙከራዎች ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን፣ አሁንም የጸረ ሙስና ትግሉ በተጠናከረ ሁኔታ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ከዚህ አንጻር የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በፌደራል ደረጃ ማቋቋምና የጸረ ሙስና ትግሉን በተደራጀ ሁኔታ መምራት ከብዙዎቹ የትግል ስልቶች ዋነኛዉ የትግል ስልት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 እንደተገለጸዉ ኮሚሽኑ ከተቋቋመባቸዉ አላማዎች መካከል የትውልድን ስነምግባር እና የሞራል እሴቶች በብቃት መገንባት፣ የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል፣ እንዲሁም ለፀረ ሙስና ትግሉ አጋዥ የሆኑ የህዝብ ንቅናቄዎችን በመፍጠር ህዝቡ የፀረ ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ቀዳሚዎች ናቸዉ፡፡ እነኚህ እና ሌሎችም አላማዎች ይሳኩ ዘንድ ኮሚሽኑ ከሚያከናዉናቸዉ ተግባራት መካከል በሥነምግባር ግንባታ እና በሙስና መከላከል ዙሪያ የተለያዩ የማሰልጠኛ ሞጁሎችን በማዘጋጀት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስልጠና መስጠት ተጠቃሽ ነዉ፡፡በዚሁ መሰረት ይህ የማሰልጠኛ ሞጁልም በየደረጃዉ ያሉ የህዝባዊ ድርጅቶች ሠራተኞችና አመራሮች የሙስናን ባህሪያት በመረዳት በተቋማቸው የሚፈጸሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን መለየትና መከላከል የሚችሉባቸውን ስልቶች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማገዝ ታስቦ የተዘጋጀ ነዉ፡፡

በዚህ ሰነድ/ሞጁል “ህዝባዊ ድርጅት” ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበን ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበን ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሃብትን የሚያስተዳደር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ነዉ፡፡ እነዚህ ህዝባዊ ድርጅቶች በአብዛኛው በባንክ፣ ኢንሹራንስ፣ ማይክሮ ፋይናንስ እና በመሳሰሉት ዘርፎች ላይ ተሰማርተው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ሲሆን፤ በሀገራችን ኢትዮጵያ በየጊዜው ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ እና ከፍተኛ ገንዘብ እና ሀብት የሚያንቀሳቅሱ ተቋማት ሆነዋል፡፡ ለሀገራዊ እድገትና የዲሞክራሲ ግንባታ ተግባራት መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦያላቸዉ ቢሆንም፤ ከዚሁ ባልተናነሰ የህዝባዊ ድርጅቶች ለህብረተሰቡ የሚያቀርቡት አገልግሎት ከመስናና ብልሹ አሰራር ጋር ተያየዞ

ይነሳል።በመሆኑም በህዝባዊ ድርጅቶች ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ተግባራትንና እና ብልሹ አሰራርሮችን በተቀናጀ እና ተቋማዊ በሆነ ሁኔታ መከላከል ግድ ይላል፡፡

ስለዚህም እንደ አንድ የግንዛቤ መፍጠሪያ አማራጭ ሆኖ ያገለግል ዘንድ ይህ የማሰልጠኛ ሞጁል ተዘጋጅቷል።ሞጁሉ በዋናነት የህዝባዊ ድርጅቶች ሰራተኞችን ግንዛቤ፣ እዉቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ከፍ በማድረግ የራሳቸዉንና የተቋማቸዉን የሙስና ተጋላጭነት በመረዳት ሙስናን የመዋጋት ትግሉን በባለቤትነት እንዲመሩ ማስቻል ነዉ። ለዚሁ ሲባል ሞጁሉ በ 3 ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ የመጀመሪያዉ ክፍል የሙስናን ፅንሰ ሀሳብ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲያስረዳ፣ ሁለተኛዉ ክፍል ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉን ተጋላጭነት እና በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችንያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ሶስተኛው ክፍል በህዝባዊ ድርጅቶች የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ጉዳት እና በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራትን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይዳስሳል፡፡

የሞጁሉ አጠቃቀምና አቀራረብ

ሞጁሉ ሲዘጋጅ በተቻለ መጠን ለሰልጣኞች ምቹ እና በስልጠና ወቅትም አሳታፊ እንዲሆን ተሞክሯል፡፡ ሰልጣኞች ከዚህ በፊት ካላቸዉ ግንዛቤና እዉቀት በመነሳት እየተወያዩና እየተከራከሩ የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ የሚረዱ የተለያዩ መልመጃዎች፣ መወያያ ነጥቦች፣ አስረጅ ናሙናዎችና ሌሎችም የስልጠና ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በእያንዳንዱ ተግባርና የስልጠና ይዘቶች የሰልጣኞች ሚና በጣም ከፍተኛ ሲሆን አሰልጣኞች ደግሞ አልፎ አልፎ ገለጻ በመስጠት እንዲሁም ዉይይቶችንና ክርክሮችን በመምራት የአመቻችነት(facilitation) ሚናቸዉን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ማለትም አመቻቾቹ ዉይይቶችን ከትምህርቱ ዓላማዎች፣ ከተሠጡት የይዘት ማብራሪያዎችና ዋና ዋና ነጥቦች አኳያ በማየት አቅጣጫ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

የማሰልጠኛ ዘዴዎች

ለስልጠናዉ አላማ መሳካት የሚከተሉት ማሰልጠኛ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ይዉላሉ፡፡

- የአእምሮ ጓዳ ማንኳኳት/Brain Storming

የአእምሮ ጎዳን ማንኳኳት ሲባል በተነሱ ቁልፍ ጥያቄዎች ዙርያ ሰልጣኞች ቀድሞ ካላቸዉ እውቀትና ልምድ በመነሳት ሃሳባቸውንና ዕይታቸዉን እንዲገልጹ የማነሳሳት ተግባር ነው።

- **ገለጻ/Presentation**

ፓወር ፖይንት (power point) በመጠቀም አሰልጣኙ የሚሰጠዉ ማብራሪያ ወይም ገለጻ ነዉ።

- **የቡድን ዉይይት/Group Discussions**

ይህ ዘዴ ሰልጣኞች በቡድን በመሆን በተነሱ ጭብጦች ዙሪያ ሃሳባቸዉንና ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ለማድረግ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው።

- አስረጅ ናሙና/Case Study

በተግባር የተፈጸሙና እንደምሳሌ የቀረቡ ጉዳዮች ሲሆኑ፣ ሰልጣኞች በቡድን በመሆን እንዲወያዩባቸዉ የሚቀርቡ ናቸዉ።

- *ታሪክ/ክስተት መናገር/Story Telling*
- *ማመሳሰል ወይም ንጽጽር /Analogy*
- *ሚና መጫወት/Role Modelling*

በአጠቃላይ አሰልጣኞች በየትምህርት ክፍሉ እንደቀረበዉ ሃሳብ፣ እንደ ተነሱት ጥያቄዎችና የስልጠና ሁኔታዎች ከላይ የቀረቡትን ዘዴዎች ሊጠቅሙ ይችላሉ፣ ሆኖም ግን አሰልጣኞች ለጉዳዩ የሚመጥን የተሻለ ስልትም መጠቀም ይችላሉ።

ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ

ይህ ስልጠና በአጠቃላይ የሚወስደው ጊዜ 12 ሰዓት ነው።

የስልጠና ሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ

ሰልጣኞች ስልጠናዉን ካጠናቀቁ በኋላ ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉን ተጋላጭነት በመረዳት፣ በህዝባዊ ድርጅቶች የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን፣ ብሎም ሙስና

በድርጅቶች ላይ ሊያደርስ የሚችለዉን ጉዳት በመረዳት፣ ለጸረ ሙስና ትግሉ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ ማስቻል ነው፡፡

መገምገሚያ ስልት

ስልጠናዉ ዉጤታማ ይሆን ዘንድ በሞጁሉ መጨረሻ ላይ አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ቼክሊስት መሰረት ስልጠናው ከመጀመሩ በፊት የቅድመ ስልጠና ግምገማ እንዲሁም ስልጠናው ሲጠናቀቅ ደግሞ የድህረ ስልጠና ግምገማ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በየክፍሎቹ መግቢያ የማነቃቂያ ጥያቄዎች እና በሁሉም ክፍሎች ማጠቃለያ ላይ የመልመጃ ጥያቄዎች በመኖራቸው ሰልጣኞች ያላቸውን ቅድመ ግንዛቤ እና ከስልጠናዉ በኋላም ያዳበሩትንና ያገኙትን የግንዛቤ እና የእውቀት ደረጃን ለመለካት እንዲያስችል ተሞክሯል፡፡

ምእራፍ አንድ

የሙስና ወንጀል ምንነት

1.1 መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀበል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው። ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል። በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎች በዚህ ምእራፍ ተካተዋል።

1.1.1 የምእራፉ ዓላማ

ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፦

1. የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
2. በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ።

1.1.2 የተፈቀደው ሰዓት

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 2፤00 ሰዓት።

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. *ከጉቦ ውጭ የምታውቋቸውን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ።*
2. *ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ።*

1.2 የሙስና ምንነት

ሙስና የሚለዉ ቃል የሚያስተላልፈዉን ትርጉም በተገቢዉ ደረጃ ተገንዘቦ አንድ ሊያስማማ የሚችል ሁሉን አቀፍና ወጥ የሆነ ትርጉም ማግኘት አስቸጋሪ ነዉ።በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን እና የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ፣ የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመሰጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል።

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፤

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል።

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ "… የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል…" በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎል።

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀለ ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል፡፡ የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎች መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ በሌላ በኩል ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

ከህዝባዊ ድርጅቶች አንፃር፣ ሙስና የድርጅቶቹን ሀብትናንብረት እንዲሁም አሰራር ለግል ጥቅም ወይም ያለአግባብ ሌሎችን ለመጥቀም የሚፈጸም ወንጀል ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡

1.3 የሙስና ዓይነቶች

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption) እና ሲስተሚክ (state capture)ተብሎ ይከፈላል፡፡

1.3.1 ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው ፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው:: መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው:: መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው::

1.3.2 ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው:: ከዚህ አኳያ የተሸሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 " ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፤-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፤ኢኮኖሚ ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል::

1.3.3 ስርዓታዊ ሙስና (systemic capture)

የሀገሪቱ አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት

ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡

ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic capture) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

1.3.4 ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

1.4 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ የሆነ ወንጀል፡፡ የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ

የሙስና ወንጀልን ለመመርመር፣ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ:: የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

1.4.1 የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ:: በዚህም ምክንያት መፈፀሙን ለማወቅ የሚያስችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ:: የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ:: ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላለዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል::

1.4.2 የሙስና ወንጀል የሚያስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማስካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መንደልን ያስከትላል:: ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል:: ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል:: ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል:: በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል::

1.4.3 የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን፤ እነዚህ ሰራተኞችና ባለስልጣት ግዴታቸውን እንዲጥሱ በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት፣ የወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው:: እነዚህ ባለስልጣናትና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው:: ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ

እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

1.4.4 በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በወንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

"የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም" የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በህዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅግ ብዙ ነዉ፡፡

1.4.5 ድንበር ተሻጋሪነቱ

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

1.5 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

1.5.1 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤

የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤

በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም

ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

1.5.2 ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ፣የተቀበለ እንደሆነበሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.5.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.5.4 አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ፣ ንብረት ጠባቂ፣ወይም አጣሪ፣ ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት)፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

1.5.5 የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃ

1.5.6 አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦

የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል።

1.5.7 በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም፦

የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም

የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

1.5.8 በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ ፣

ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም

በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.5.9 በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

1.5.10 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.5.11 ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል

በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

1.5.12 ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

1.5.13 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 2)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤

ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.5.14 የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.5.15 መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፡፡

አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.5.16 መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

1.5.17 ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠይቅም፡፡

1.5.18 ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.5.19 ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣ያገናኘ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

1.5.20 በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤

ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፡፡

1.5.21 በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ

ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል።

ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል።

1.5.22 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል።

1.5.23 ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም።

1.5.24 ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ።

1.5.25 በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. "ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት" በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤
2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. "ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል" ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

ምእራፍ ሁለት

ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉ ተጋላጭነት እና በሕዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች

2.1 መግቢያ

የሙስና ወንጀል በማንኛውም መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና በተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸም ቢሆንም ከገንዘብ ዝውውር ጋር ከፍተኛ ትሥሥር ባላቸው ህዝባዊ ድርጅቶች (በባንኮች፣ በመድኅን ድርጅቶችና መሰል የፋይናንስ ተቋማት) ግን መቆጣጠር በሚያዳግት አኳኋን እየተስፋፋ ይገኛል፤ በተለይም "በውስጥ ሰራተኞች" አማካኝነት የሚፈጸም ሲሆን እጅግ በጣም ዉስብስብ ይሆናል (ፍትሕ ሚኒስቴር፣ 2014)።

በዚህ መሰረታዊ ሀሳብ መነሻነት በዚህ ምእራፍ የመጀመርያዉ ክፍል ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉን ተጋላጭነት የሚዳስስ ሲሆን የብድር አሰጣጥ፣የህግ ተገዢነት፣የደንበኛ/ተገልጋይ መስተጋብር፣ የሰነድ/መረጃ አየያዝና አጠቃቀም፣ እና የመሳስሉትን በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል።በተጨማሪም የምእራፉ ሁለተኛዉ ክፍል በህዝባዊ ድርጅቶች የሚከሰቱ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በጥልቀት ለመዳሰስ ሞኩሯል። ሰልጣኞች በድርጅቶቻቸዉ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችን እና የሙስና ወንጀሎችን መለየት ሲችሉ የድርጅት፣ የመንግስትና የህዝብ ኃብት እንዳይመዘበር የመከላከልና የመጠበቅ ሚናቸውን በአግባቡ ይወጣሉ።

2.1.1 የምእራፉ ዓላማ

የዚህ ምእራፍ ስልጠና ሲጠናቀቅ ሰልጣኞች፤

1. ህዝባዊ ድርጅቶች በአጠቃላይ፣ በተለይ የሚሰሩበት ድርጅት ለሙስና ያለዉን ተጋላጭነት ይገነዘባሉ፤
2. በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸሙትን/የሚታዩትን ዋና ዋና የሙስናና ኢስነምግባራዊ ድርጊቶችን ይለያሉ፤
3. ዋና ዋና የሙስናና ኢስነምግባራዊ ድርጊቶችን ከራሳቸዉ ድርጅት አንጻር ይተነትናሉ፤
4. ድርጅቱን እና እራሳቸዉን ከሙስናና ብልሹ አሰራር ይከላከላሉ።

2.1.2 ለምእራፉ የተሰጠው ሰዓት

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 5፡00 ሰዓት ነው፡፡

2.1.3 የምእራፉ አቀራረብ

በዚህ ክፍል የቡድን ዉይይት/Group discussions፣ ታሪክ መናገር/Story telling፣ አስርጂ ናሙና/cases እና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም ሰልጣኞች ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉ ተጋላጭነት በሚመለከት የተለያዩ ሀሳቦች እንዲያንጸባርቁ እና በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ይደረጋል፡፡ እንደመነሻም የስልጠናው አመቻቾች አጭር ገለጻ/Presentations/ ያደርጋሉ፡፡

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለሌሎች ተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. ህዝባዊ ድርጅቶችን ከሌሎች ዘርፎችና ድርጅቶች በተለየ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጧቸው የሚችሉ አሰራሮች/ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

2. ህዝባዊ ድርጅቶችን ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ ከሚችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ሁለቱን በመምረጥ ያብራሩ፡፡

3. በህዝባዊ ድርጅቶች የሚታዩ/የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

2.2 ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉ ተጋላጭነት

2.2.1 የብድር አሰጣጥ፣ ክትትልና አከፋፈል ሁኔታ

? *የብድር ሂደት በምን መልኩ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል? መልሱን ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡*

በብድር አሰጣጥ፣ ክትትልና አከፋፈል ላይ የብድር አሰጣጥ ሂደት መጓተት፣ የገንዘብ እጥረትና ተደራሽ ዓለመሆን የራሳቸው አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ቢሆንም፣ በዚህ ረገድ ለሚፈጠር ችግር ሙስና ከፍተኛዉን ድርሻ ይወስዳል። በመሆኑም ከብድር ማረጋገጫ ሂደቶች፣ ከብድር ክትትልና አከፋፈል ጋር በተያያዘ ህዝባዊ ድርጅቶች ለሚከተሉት ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊጋለጡ ይችላሉ።

የባንክና የማይክሮ ፋይናንስ ሰራተኞች በብድር አሰጣጥ ረገድ የተበዳሪዎችን ቅደም ተከተል በማዛነፍ፣ በተጭበረበረ ወይም ባልተሟላ መረጃ ተመስርተው ወይም ተበዳሪው መያዣ ሳያቀርብ ብድርን በመፍቀድ እና ኮሚሽን ለመቀበል በመመሳጠር ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶች ላይ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይችላል። ብድር አመላለስን በተመለከተ በፋይናንስ ሴክተሩ ያሉ ሰራተኞች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ፣ ብድሮች በሰዓቱና በአግባቡ እንዳይመለሱ፣ በመያዣነት የተያዙ ንብረቶችም ለብድሩ መሸፈኛ እንዳይዉሉ ወይም በርካሽ ዋጋ እንዲተላለፉ በመመሳጠር ስነምግባር በጎደለው ተግባር ዉስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ።

ከላይ የተጠቀሱ ሁኔታዎች እንዲከሰቱ የብድር ፖሊሲ ጠቅለል ባለ መልኩ መቀመጥ አንዱ መንስኤ ሲሆን፣ መተንተን እና መተርጎም የሚገባቸውን ነገሮች በዝርዝር የሚያስቀምጥ ማኑዋል/procedure/ አለመኖር/አለመዘጋጀት ደግሞ ሌለኛዉ ምክንያት ነው። ለምሳሌ ያህል በልዩነት የሚታዩ ጉዳዮች በዝርዝር ምን ምን መሆን እንደሚገባቸው ግልፅ በሆነ መልኩ ካልተገለጸ የግልፅነት እና የተጠያቂነት ክፍተት ያስከትላል፤ በግለሰብ ውሳኔ ላይ የተመሰረተ አሰራር ወይም ውሳኔ እንዲኖር በማድረግም ለሙስናና ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል። (የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ.የአሰራር ስርዓት ጥናት ሪፖርት፣ 2004)። እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎች ደግሞ ከፍትሃዊነት ይልቅ በግላዊ ግንኙነቶች ተጽእኖ ስር ሊወድቁ ስለሚችሉ ፍትሃዊ ያልሆነ የብድር ስርጭትን ያስከትላሉ። በሌላ መልኩ እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎችና ድርጊቶች ተበዳሪዎችን ግልጽ ላልሆኑ እና ላልተገቡ ክፍያዎች ከመዳረግም በላይ፣ ከዕዳ አዙሪት ውስጥ እንዳይወጡ ሊያደርጓቸዉ ይችላሉ። በዚህ መልኩ ተጋላጭ የሆኑ አካላት ሊበዘበዙ ይችላሉ።

2.2.2 የህግ ተገዢነት እና ቁጥጥር ስርዓት (Compliance and Regulatory Oversight)

? *የህግ ተገዢነትና የቁጥጥር ስርዓት እንዴት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል?መልሱን ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡*

የሰራተኞች የህግ ተገዢነት እና የህግ ቁጥጥር ሰርዓት መላላት ተቋማትንና አሰራራቸዉን ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በየቅርንጫፉ ከህዝብ የሚሰበሰበዉን የቁጠባ ገንዘብ በመመሳጠር ለግል ጥቅም ማዋል፤ሲፒኦ (CPO) እና የዋስትና ሰነዶችን ጠያቂዉ አካል በባንኩ በቂ ገንዘብ ሳይኖረዉ እንዳለዉ አድርጎ የሀሰት ሰነድ በመስጠት ለግል ጥቅም መደራደር፤ የሚስጥር ቁልፍ በመቀበል/ማቀበል የደንበኞችን ተቀማጭ ገንዘብ መዝረፍ፣ እና የመሳሰሉ ሰነምግባር የጎደላቸዉ ተግባራት በህግ ተገዢነት እና ቁጥጥር ሰርዓት መላላት ሊከሰቱ የሚችሉ ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም ሰራተኞች ለግል ጥቅም ወይም ሌላ ሰው ለመጥቀም ሲሉ የተጭበረበረ ወይም ሀሰተኛ የሂሳብ ደብተር የመክፈት ወንጀል ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል የደንበኞች የቁጠባ ሂሳብ እንቅስቃሴን መቆጣጠሪያ እና መከታተያ ስርዓቱ በራሱ ለሙስና ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በብዙ ባንኮች የደንበኞች የቁጠባ ሂሳብ inactive ሳይሆን ረጅም ጊዜ ማለትም ሁለት ዓመት ስለሚቆይ ይህን በመጠቀም ሂሳቡን ሌሎች (የሂሳቡ ባለቤት ያልሆኑ) ግለሰቦች በማንቀሳቀስ ወይም ያለውን የገንዘብ መጠን ወደሌላ የቁጠባ ሂሳብ በመውሰድ ለግል ጥቅም ሊውል የሚችልበትን ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡ (የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ.የአሰራር ስርዓት ጥናት ሪፖርት፣ 2004) ፡፡

ሰራተኞች በስነ-ምግባር ደረጃዎች እና የህግ ተገዢነት ላይ ተገቢውን ስልጠና ላይኖራቸውም ስለሚችል ላልታሰበ የስነምግባር ጉድለት ሊዳርጋቸዉ ይችላል፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ስልጠና አለመስጠት ሰራተኞች የብልሹ አሰራርን መዘዝ እንዳይገነዘቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እና ግብዓቶች ለሠራተኞች በቂ አለመሆን፣ የተሳሳተ ሪፖርት እንዳይደረግ ወይም መረጃ እንዳይደበቅ የሚያስችል ቁጥጥር አለመኖር ወይም ደካማ መሆን፣ ብልሹ

አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችሉ የቁጥጥር ማዕቀፎች አለመኖር እና ለህግ ተገዥ ያልሆኑ ሰራተኞችን ተጠያቂ የሚያደርግ አሰራር አለመኖር ወይም አለመተግበር በዚህ ረገድ ለሚፈጠር ተጋላጭነት ዋነኛ መንሳኤዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ደንቦቹን በመተላለፍ ወይም አታላይ ተግባራትን በመፈፀም ተወዳዳሪነትን ለማግኘት ሊሞክሩ ይችላሉ፣ ይህ ግን የሕግ መዘዞችን የሚያስከትል እና የደንበኞችን እምነትም አደጋ ላይ የሚጥል ነዉ።

አስረጅ ናሙና/Case Study 1

ከዚህ ቀጥሎ ከፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ ምንጭ የተገኘ ኬዝ ቀርቦላችኋል፤ ኬዙን ካነበባችሁ በኋላ ቀጥለዉ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ተወያዩባቸው።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ወሎ ሰፈር አካባቢ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይድነቃቸው ቅርንጫፍ፣ ሦስት የባንኩ ሰራተኞች ከአንድ ተባባሪያቸው ጋር በመሆን የማጭበርበር ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው በመጠርጠራቸው በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ መቀጠሉን የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ገልጿል።ተጠርጣሪዎቹ ከሌሎች ግብረ አበሮቻቸው ጋር በመሆን ለረጅም ጊዜ ያልተንቀሳቀሱ የባንኩን ደንበኞች ሂሳብ በማጣራትና ሀሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት ከአንዲት የባንኩ ደንበኛ 1 ሚሊዮን 8 መቶ ሺህ ብር እና ከሌላኛው የባንኩ ደንበኛ ደግሞ 2 ሚሊዮን 76 ሺህ ብር በአጠቃላይ ከሁለቱ የባንኩ ደንበኞች እውቅና ውጭ 3 ሚሊየን 876 ሺህ ብር ወደ ሌላ ግለሰብ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ገንዘቡን እንደተከፋፈሉት ፖሊስ በምርመራ ማረጋገጡን አስረድቷል። የግለሠቦቹ የባንክ ሂሳብ ለረጅም ጊዜ የማይንቀሳቀስ መሆኑን ለባንኩ ሰራተኞች መረጃ ሲሰጡ የነበሩ እና የጥቅም ተካፋይ የሆኑ 3 ተጠርጣሪዎችን ለመያዝም ክትትል እየተደረገ መሆኑን የፖሊስ መረጃ ያሳያል። ሰራተኞቹ ድርጊቱን እንደፈፀሙት አመላካች ማስረጃዎች እየተገኙ መሆኑን ያስረዳዉ የፖሊስ ሪፖርት፥ ግለሰቦቹ ህዝብና መንግስት የጣለባቸውን ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው የማይገባ ተግባር መፈፀማቸው ህብረተሰቡ በባንኮች ላይ ያለውን አመኔታ የሚያሳጣ በመሆኑ የመንግስትም ሆነ የግል

ባንኮች በሰራተኞቻቸው ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ እንደሚገባም ተጠቁሟል። (የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ ሐምሌ 23/2016)።

1. ከላይ ስለቀረበው ጽሁፍ ሰምተው ይሆን?
2. እንደዚህ አይነት የማጭበርበር ወንጀል እርስዎ በሚሰሩበት ተቋምስ ተከስቶ ያውቃል? ተቋምዎ ለእነዚህ አይነት ወንጀሎች ተጋላጭ ነው ብለው ያስባሉ? እንዴት?

2.2.3 የደንበኛ/ወኪሎች መስተጋብር

? *የደንበኛ/ወኪሎች መስተጋብር በምን መልኩ ለሙስና ሊያጋልጥ ይችላል?መልሱን ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ።*

ሰራተኞች ከተገልጋይ/ደንበኛ ወይም ከወኪሎቻቸዉ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ምክንያት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊጋለጡ ይችላሉ። ከዚህ ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች ለመጠነ ሰፊና ፈርጀ ብዙ የሙስና ችግሮች መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ በመድን ድርጅቶች እነዚህ ችግሮች ቀጥታ ከሶስተኛ ወገን አቅራቢዎች፣ ከወኪሎችና ደላሎች ጋር ከሚደረግ ግንኙነት ጋር የሚገናኙ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህም በሚከተሉት ምሳሌዎች ሊብራራ ይችላል።

ወኪሎች ደንበኞችን ለመመልመል ጥቅማጥቅሞችን በማጋነን ወይም የሚያጋጥሙትን ስጋቶች በማሳነስ ከሥነ ምግባር ውጭ የሆኑ ድርጊቶች ዉስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ። በሌላ መልኩ አማካሪዎች እና ወኪሎች ደንቦችን ለማቋረጥ ወይም ብልሹ ድርጊቶችን ለመፈጸም ሶስተኛ ወገኖችን አላግባብ ሊጠቀሙ ይችላሉ። ወኪሎች አንዳንድ ምርቶችን በሌሎች ላይ እንዲሸጡ ማበረታቻ ሊደረግላቸው ይችላል፣ ይህም ወደ የጥቅም ግጭት ያመራል። የመልስ ምት ወይም ያልተገለፀ ኮሚሽን ይህንን ጉዳይ የበለጠ ሊያባብሰው ይችላል። በሌላ በኩል በዳኝነት ግምገማ ወይም ከተወካዮች ጋር በመመሳጠር የአደጋ መንስኤዎችን በማሳሳት ፍትሃዊ ያልሆነ የዋጋ አወጣጥ ወይም ሽፋንን ውድቅ የማድረግ አዝማሚያ ሊታይ ይችላል።

በኢንሹራንስ/መድን አሰራር የይገባኛል ጥያቄ ሂደት ለማጭበርበር ተግባር የተጋለጠ ነው። ማለትም ሰራተኞች የተጋነኑ ወይም/እና የውሸት የይገባኛል ጥያቄዎች ሲቀርቡላቸው ጥያቄዎቹን

በመቀበልና እንዲሁም ህጋዊ የይገባኛል ጥያቄዎችን ውድቅ በማድረግና ክፍያዎችን በመቀነስ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ የሚወስዷቸው እርምጃዎች የዘርፉን ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት እንዲጨምር ያደርጋሉ:: ኩባንያዎች ብዙውን ጊዜ በሶስተኛ ወገን አቅራቢዎች እንደ የይገባኛል ጥያቄ ማስተካከያ ወይም የደንበኛ አገልግሎት ባሉ አገልግሎቶች ይተማመናሉ:: እነዚህ ሶስተኛ ወገን አቅራቢዎች ብልሹ አሰራር ውስጥ ከተሳተፉ፣ ሙስና በኢንሹራንስ/መድን ሰጪው ላይ በደንብ ሊንፀባረቅ ይችላል::

2.2.4 የሰነድ አያያዝና አጠቃቀም

? *የሰነድ አያያዝና አጠቃቀም እንዴት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል?መልሱን ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ::*

ከመረጃ ወይም ሰነድ አያያዝ ጋር በተያያዘ የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች ለሙስና ሊጋለጡ የሚችሉባቸው ብዙ አጋጣሚዎች ይኖራሉ፤ ከእነዚህም መካከል ከታች የሰፈሩት ሁለት ወሳኝ ነጥቦች እንደ ጥሩ ማሳያ ሊወሰዱ ይችላሉ::

2.2.4.1 የመዝገብ/ሰነድ አያያዝ

ለሙስና ሊጋለጡ ከሚችሉ አደገኛ ሁኔታዎች አንዱ የመዝገብ/ሰነድ አያያዝ ነው:: መዝገብ ቤትን ህገ ወጦች በቀላሉ እንዲገለገሉበት እና እንደፈለጉ እንዲጠቀሙበት ማድረግ ፋይሎች እንዲሰረቁ፣ እንዲጠፉ፣እንዲደበቁ፣ እንዲቀየሩና እንዲበላሹ ሊያደርግ ይችላል:: ለምሳሌ የብድር ሰነዶች በአግባቡ የማይቀመጡ ከሆነ ለሙስና ወንጀል በር ሊከፍቱ ይችላሉ:: ይህ ማለት የተበዳሪዎችን አጠቃላይ መረጃ የሚይዘው ሰነድ ደህንነቱ በተጠበቀና በቀላሉ ሊገኝ በሚችልበት መልኩ ሊቀመጥ ሲገባ፣ በተቃራኒዉ ደህንነቱን ባልጠበቀና ፋይሉ ምን ቦታ ላይ እንደተቀመጠ ለማወቅ በሚያስቸግር፤ እንዲሁም ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለመቆጣጠር እና ለመከታተል በሚያስቸግር መልኩ ከተቀመጠ ሊጠፋ የሚችልበትን ክፍተት ሊፈጥር ይችላል:: ይህ ደግሞ ብድር ስለተሰጣቸው ግለሰቦችና ተቋማት፣ እንዲሁም የነበረውን ሂደት ለማየት አስቸጋሪ የሚሆንበትን ሁኔታ በመፍጠር ለሙስና ሊያጋልጥ ይችላል::(የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ.የአሰራር ስርዓት ጥናት ሪፖርት፣ 2004)::

አስረጅ ናሙናዎች/Case Studies 2&3

ከዚህ ቀጥሎ ከፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ ምንጭ የተገኙ ሁለት ኬዞች ቀርበዉላችኋል፤ ኬዞቹን ካነበባችሁ በኋላ ቀጥለዉ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያዩባቸው።

1. በኢይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ፋብሪካ ያገለገሉ መሳሪያዎችን የጥራት ደረጃ ለመገምገም እና የዋጋ ግምት የተሰራባቸውን ሰነዶች ለማግኘት፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመመልከት ሁሉንም አቃፊ ፋይሎች መፈተሽ ያስፈለገ መሆኑን እና ይህንንም ለማግኘት ብዙ ጊዜያትን የፈጀ እንደነበር የፌደራል ስነምግባርና ጸረሙስና ቡድን አረጋግጧል።

2. በ የኤልሴ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ፋብሪካ፣ የመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ፣ የሼባ ቆዳ ፋብሪካ እና የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካም እንዲሁ አብዛኛዎቹ ሰነዶች ቅደም ተከተላቸውን ይዘው ያልተቀመጡ በመሆናቸውና የሚፈለጉ ሰነዶች የትኛው አቃፊ ፋይል ውስጥ እንደሚገኙ በግልፅ የማይታወቁ በመሆናቸው ምክንያት ሰነዶች ለማግኘት አስቸጋሪ ሁኔታን የፈጠረ እንደነበር በፌደራል ስነምግባርና ጸረሙስና መርማሪዎች ቡድን ተገልጿል። (የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ.የአሰራር ስርዓት ጥናት ሪፖርት፣ 2004)።

1. ከላይ የተገለጹት የመረጃ/ሰነድ አያያዝ ግድፈቶች እርስዎ በሚሰሩበት ድርጅት አጋጥሞዎት ያውቃል? 2. ድርጅቱ ለእነዚህ አይነት ግድፈቶች ተጋላጭ ነው ብለው ያስባሉ?

2.2.4.2 የኢንፎርሜሽ ቴክኖሎጂ እና የውሂብ/Data አስተዳደር

በቂ ያልሆነ የሳይበር ሴኪዩሪቲ እና የዳታ አስተዳደር ስርዓት፣ የደንበኞችን መረጃ በማጋለጥ የግል መረጃዎችን ለተጭበረበረ ዓላማ አላግባብ መጠቀምን ያስከትላል። ደካማ የመረጃና

ቴክኖሎጂ ስርዓት የማጭበርበር ድርጊቶችን ለመፈጸምና ለመደበቅ በር ይከፈታል። በተለይም ደግሞ የዲጂታል ብድር ስርዓት እየተስፋፋና እያደገ ሲሄድ ስርዓቶች አስተማማኝ ካልሆኑ የማጭበርበር እና የመጭበርበር እድልን ይጨምራል።

አስረጅ ናሙና/Case Study 4

ከዚህ ቀጥሎ ከገብረእግዚአብሔር፣ መሰረትና ቶማስ ምንጭ የተገኘ ኬዝ ቀርቦላችኋል፤ ኬዙን ካነበባችሁ በኋላ ቀጥለዉ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ተወያዩባቸው።

እ.ኤ.አ. በ2019 አደይሚ አደርሚ አብዱልራፊእ የተባለው አንድ ናይጀሪያዊና ሌሎች አምስት ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይ ስድስት ግለሰቦች ሀሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያና ሌሎች ተያያዥ ሰነዶችን በመገልገል ከአንድ አሜሪካዊ ግለሰብ "ዓለም አቀፍ የገንዘብ ማስተላለፊያ ሲስተምን" ("Wire Transfer") ተጠቅመው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፊንፊኔ ቅርንጫፍ ላይ በአጠቃላይ 110 ሚሊዮን ዶላር አጭበርብረው ለመውሰድ በማሰብ እንቅስቃሴ መጀመራቸው፤ በመጨረሻም 60,990,939 (ስልሳ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ) ብር አውጥተው ከወሰዱ በኋላ በብሔራዊ የመረጃና ደሕንነት አገልግሎት ክትትል እጅ ከፍንጅ መያዛቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ሚዲያዎች መዘገቡንና በእነዚህ ግለሰቦች ላይ የወንጀል ክስ የተመሰረተ መሆኑን ይታወቃል። (ምንጭ፦ News Business Ethiopia, በገብረእግዚአብሔር፣ መሰረትና ቶማስ፣2014 እንደተገለጸዉ)።

1. ከላይ የተገለጸዉ ወንጃል እርስዎ በሚሰሩበት ድርጅስ አጋጥሞዎት ያውቃል?
2. ድርጅቱ ለእንደዚህ አይነት ግድፈቶች ተጋላጭ ነው ብለው ያስባሉ?

2.2.5 አስተዳደራዊ ተጋላጭነት

? *አስተዳደራዊ ተጋላጭነት ሲባል ምን ማለት ነዉ? መልሱን ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ።*

ግልጽ ያልሆኑ አስተዳደራዊ ተግባራትና አስተዳደራዊ ድክመቶች ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስናተጋላጭ እንዲሆኑ ጉልህ ድርሻ ይኖራቸዋል። ደካማ የአስተዳደራዊ መዋቅር እና በድርጅት ውስጥ የተጠያቂነት እጦት፣ ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት የሚታለፍበትን ሁኔታ ይፈጥራል። በሌላ በኩል ግልጽ የሆነ የተግባር መለያየት አለመኖር አንዱ ተጋላጭነትን የሚያበረታታ ሁኔታ ሲሆን፤ ሚናን በበቂ ሁኔታ አለመለየት የማጭበርበር ድርጊቶችን መቆጣጠር ሳይቻል እንዲቀር ያደርጋል።

ልዩ ልዩ ደንቦችና መመሪያዎች አለመኖር፤ ያሉትም ግልጽነት የጎደላቸው መሆን የሙስናን ተጋላጭነት የሚያባብሱ ምክንያቶች ናቸው። በተጨማሪም የፍላጎት ግጭትን በመፍጠር ሰራተኞች በድርጅቱ ወይም በደንበኞቹ ወጪ ራሳቸውን የሚጠቅሙ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ።

ከሰራተኛ ቅጥር ጋር በተያያዘ ማለትም ሰራተኞችን መመልመል፣ መቅጠር፣ እና እድገት መስጠት ላይም ተገቢ የሆኑ ስርዓቶች፣ ህግና ደንቦች እየታወቁ ሲጣሱ ይስተዋላሉ። ከእነዚህም ውስጥ ቅጥርን በዝምድናና ቀረቤታ፣ እና በጉቦ መፈጸም ይገኙበታል። ምቹ የሥራ ሁኔታዎችን አለመፍጠርም በድርጅቱ ብልሹ አሰራሮች እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይችላል።

በሌላ መልኩ የሰራተኛ ባህሪ ላይ ተጽእኖ የሚኖራቸዉ ተግባራት ለምሳሌ ከመጠን በላይ አስጨናቂ የሆኑ ኢላማዎችና ባህላዊ ልማዶች የሙስና ተጋላጭነትን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከፍተኛ ጫና የሚፈጥሩ የሽያጭ ኢላማዎች እና የአፈጻጸም መለኪያዎች ሰራተኞች ግቦችን ለማሳካት ሲሉ ስነምግባር የጎደለው ባህሪ ዉስጥ እንዲሳተፉ ሊያበረታታቸዉ ይችላል።

ጫና የበዛበት የምልመላ ስልቶች ደግሞ ደንበኞች ያለ ፍላጎታቸው የተቋሙ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ከአቅማቸው በላይ እንዲበደሩ ሊገፋፋቸው ይችላል። በአጠቃላይ ትርፍን የሚያስቀድም እና ሥነ ምግባር የጎደላቸው ድርጊቶችን የሚታገሥ አልፎ ተርፎም የሚሸልም ድርጅታዊ ባህል በሠራተኞች መካከል ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊትን ያበረታታል ብሎም ወደ ከፋ የሙስና ወንጀል ያመራል።

የቡድን ዉይይት

እርስዎ በሚሰሩበት ድርጅት ለእነዚህ አይነት አስተዳደራዊ ግድፈቶች ተጋላጭ ነው ብለው ያስባሉ? መልሱን በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

2.2.6 የዉስጥ ቁጥጥርና ኦዲት

? *የወስጥ ቁጥጥርና ኦዲት እንዴት ለሙስናሊያጋልጥ ይችላል? መልሱን ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡*

የድርጅት ዉስጣዊ የቁጥጥርና ኦዲት ሁኔታ ስነምግባር ለጎደለዉ ተግባርና ለሙስና ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ በቂ ያልሆነ ክትትል/ሱፐርቪዥን እና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር አለመኖር ብልሹ አሰራሮች እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በቂ ያልሆኑ የቁጥጥር ስርዓቶች ወይም ደካማ የውስጥ ኦዲት ጉድለቶችን ለይተው ማሳወቅ ይሳናቸዋል፤ ምክንያቱም ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃ መስጠት ስለማይችሉ፣ ብልሹ ድርጊቶች ቁጥጥር ሳይደረግባቸውና ሳይስተዋሉ እንዲቀጥሉ ያደርጋሉ፡፡ በቂ ያልሆነ የግብይቶች ክትትልም ህገወጥ የገንዘብ ፍሰትን በማመቻቸት የሙስና ወንጀል እንዲጎለብት አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

2.2.7 ሌሎች የተጋላጭነት ሁኔታዎች

? *ከላይ በዝርዝር ከተብራሩት የተጋላጭነት ሁኔታዎች በተጨማሪ ለሙስና ሊያጋልጡ የሚችሉ ሌሎች ሁኔታዎች ምን ሊሆኑ ይችላል? መልሱን ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡*

ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር

ሰራተኞች እንዲሁም ሀላፊዎች ህገወጥ የገንዘብ ዝዉዉርን፣ በህገ ወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብን አመጣጥ በመደበቅ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፣ ለዚህም ብዙ ጊዜ ውስብስብ ግብይቶችን በበርካታ አካውንቶች ውስጥ ያካሂዳሉ።

የስጋት አስተዳደር

በስጋት አመራር ወቅት የስጋት ምዘናዎችን ማዛባት፣ ማለትም ብድሮችን ለማመቻቸት የተበዳሪውን የብድር ብቃት ከመጠን በላይ መግለጽ፤ በቂ ያልሆነ ትጋት፣ ማለትም በተበዳሪዎች ላይ በተለይም ከፍተኛ ተጋላጭነት ባላቸው ዘርፎች ላይ ጥልቅ ምርመራ አለማድረግ።

የገበያ ስርዓት

ከገበያ ሁኔታ ጋር በተየያዘ የውስጥ ንግድ ማለትም ሚስጥራዊ መረጃን ለግል ጥቅም መጠቀም፤ የወለድ መጠኖችን ወይም ክፍያዎችን ለመቆጣጠር ከሌሎች ባንኮች ጋር በመተባበር፣ ወዘተ ሰራተኞች ከሚሳተፉባቸዉ የስነምግባር ጉድለቶች መካከል ሊጠቀሱ ይችላሉ። ይፋዊ ያልሆኑ መረጃዎችን የማግኘት መብት ያላቸው ሰራተኞች የዋስትና ህጎችን በመጣስ በመረጃው ላይ ተመስርተው የዋስትና ሰነዶችን ሊገበያዩ ይችላሉ።

የግብይት እና ማስታወቂያ አተገባበር

አሳሳች የማስታወቂያ አሰራር ደንበኞች ፍላጎታቸውን የማያሟሉ ፖሊሲዎችን እንዲገዙ ያደርጋል።

ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ

ፖለቲካዊ ግንኙነቶችን በመጠቀም ተስማሚ አያያዝን ወይም ውሎችን ለማስጠበቅ፤ እንደዚሁም በተቆጣጣሪዎች ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽእኖ በመፍጠር ሕጎች ያለ አግባብ እንዲፈጸሙ ሊደርግ ይችላል።

2.3 በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች

ባንኮችን፣ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን (MFIs) እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎችን ጨምሮ በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ሥነ ምግባር የጎደላቸው ድርጊቶች የተለያየ መልክ ሊኖራቸው ይችላል። ከብዙዎቹ የተወሰኑትን ብቻ ከታች በተመለከተዉ አግባብ ለማብራራት ተሞክሯል።

2.3.1 ጉቦ

አዋጅ ቁ 881/2007 እንደሚደነግገው ማንኛውም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በሀላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ሳለማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ/የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ/የሰጠ ከሆነ ድርጊቱ እንደ ጉቦ ወንጀል ይወሰዳል። ለምሳሌ የባንኮችና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ሰራተኞች ብድር የሚጠይቁ ደንበኞችን ያለ ቅደም ተከተላቸው የጥቅም ተጋሪ በመሆን ብድር እንዲፈቀድላቸው ሊያደርጉ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል የባንክ ሀላፊዎች/ሰራተኞች መሥፈርቶችን የማያሟሉ ብድሮችን ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት ወይም ለማጽደቅ ከደንበኞች ጉቦ ሊቀበሉ ይችላሉ። ተበዳሪዎችም ብድር ለማግኘት ጉቦ ሊሰጡ ይችላሉ፣ ይህም የብድር አሰጣጥና አመላለስ ሂደቱን ታማኝነት ይጎዳል። የባንክ ኃላፊዎችም ብድሮችን በማጽደቅ ከሦስተኛ ወገኖች ጉቦ ሊቀበሉ ይችላሉ።

2.3.2. ማጭበርበር

ማጭበርበር ማንኛውም ጥቅምን ለማስጠበቅ ሲባል የሚፈጸምን ኢ-ፍትሃዊ ወይም ህገወጥ አታላይ ተግባርን ይገልጻል። ለምሳሌ የፋይናንስ ምርቶችን በተሳሳተ መንገድ ማቅረብ፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎችን በተደበቁ ክፍያዎች ወይም አደጋዎች መሸጥ፣ ወዘተ።

አስረጅ ናሙና/Case Study 5

ከዚህ ቀጥሎ ከፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ ምንጭ የተገኘ ኬዝ ቀርቦላችኋል፤ ኬዙን ካነበባችሁ በኋላ ቀጥለዉ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ተወያዩባቸው፡፡

የባንክ አሰራር ሥርዓትን ለማስተካከል በሚል የግለሰቦችን ምስጢር ቁጥር በመውሰድ ገንዘብ ያጭበረበረው ተከሳሽ በእስራት ተቀጣ፡፡ የፍትሕ ሚኒስቴር የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ባቀረበው ክስ ዝርዝር ላይ ተከሳሹ በአዲስ አበባ ከተማ በ2015 ዓ.ም በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ 6 ግለሰቦች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንደተደወለ በማስመሰልና የንግድ ባንክ የአሰራር ሥርዓት በማስተካከል ሥራ ላይ እንደሆነ በመግለጽ የግለሰቦችን የምስጢር ቁጥር እንዲነግሩት በማድረግ ከ370 ሺህ ብር በላይ ገንዘብ ማጭበርበሩ ተመላክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኝ የቅጣት አስተያየቶችን በመያዝ ተከሳሹን በ6 ዓመት ከ6 ወራት ጽኑ እስራት እና በ6 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑን የኤፍቢሲ ዘገባ ያሳያል፡፡(የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ የካቲት 21/2016)፡፡

1. ከላይ ከተጠቀሰው አስረጂ ናሙና ምን መረዳት ይቻላል?
2. ይህንን የማጭበርበር ወንጀል ማን/በምን መደብ ያለ ባለሙያ ሊፈጽመዉ ይችላል?
3. እርስዎ በሚሰሩበት ድርጅት ውስጥ በእንደዚህ አይነት ወንጀል ተጠያቂ ሆኖ የሚያውቅ ሰራተኛ አለ?

2.3.3 ምዝበራ

ምዝበራ ማለት አንድ የህዝብ ድርጅት ሰራተኛ በአደራ በተሰጠው እቃ ወይም ንብረት ያለአግባብ ሲጠቀም ወይም በንብረቱ ሲያዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰራተኛ ከደንበኛ አካውንት ለግል ጥቅም ሲል ገንዘብ አውጥቶ ሊጠቀም ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ አንድ ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ እቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ጥሬ ገንዘቦችን የመውሰድ ወይም የመሰወር ተግባር ላይ ሊሰማራ ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የባንክና ማይክሮ ፋይናንስ ሰራተኞች ከቁጠባ የሚገኘን ወለድ እንዲሁም ትርፍ ለደንበኞች በጊዜው አለማሳወቅ፣ ደብተር ላይ አለመመዝገብ እና ወደ ራስ ሂሳብ በማዛወር መጠቀም ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

አስረጅ ናሙና/Case Study 6&7

ከዚህ ቀጥሎ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ ሁለት ኬዞች ቀርቦዉላችኋል፤ ኬዞቹን ካነበባችሁ በኋላ ቀጥለዉ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ተወያዩባቸው።

1. *በኢንተርኔት ባንኪንግ ከባንኩ ደንበኛ ከሆኑት ግለሰብ ላይ ከ1.5 ሚሊዮን ብር በላይ አጭበርብረዋል በሚል ወንጀል የተጠረጠሩት ሦስት የአዋሽ ባንክ የለገጣፎ ቅርንጫፍ ሰራተኞች ክስ ተመሰርቶባቸዋል። የአቃቢ ህግ ክስ እንደሚያስረዳው ተከሳሾቹ በአዋሽ ባንክ ወገልዎ ቅርንጫፍ ሰራተኛ ሆነው እየሰሩ፣ የአዋሽ ባንክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ደንበኛ ከሆኑት ወ/ሮ ፀሀይነሽ አበጋዝ ልዩ የጎልማሶች ቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ደንበኛዋ በማያውቁት እና የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚም ባልሆኑበት ሁኔታ በባንኩ ደንበኛ ላይ ተጠርጣሪዎቹ የማጭበርበር ወንጀሉን ፈጽመዋል። በቀን ጥቅምት 08/2016 1ኛ ተከሳሽ ደንበኛዋ ሂሳብ ሲከፍቱ ያስመዘገቡትን የእጅ ስልክ ቁጥር ወደ ሌላ ስልክ ቁጥር በመቀየር አጭር የፅሁፍ መልዕክት እንዳይደርሳቸው በማድረግ፣ 2ኛ ተከሳሽ የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት መጠቀሚያ ሂሳብ በኮምፒውተር የይለፍ ቃላቸው በመክፈት፣ 3ኛ ተከሳሽ የተደረገውን የስልክ ቁጥር ለውጥና የተከፈተውን የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት መጠቀሚያ ሂሳብ አስፈላጊውን ማጣራት ሳያደርግ በማፅደቅ በደንበኛዋ ስም የኢንተርኔት ባንኪንግ ሂሳብ ከፍተዋል ይላል ክሱ። በአጠቃላይ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተሳታፊ በመሆን ለራሳቸው ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም በማስገኘት አላማ የተሰጣቸውን ሃላፊነት ያለአግባብ በመገልገል፣ ጠቅላላ ብር 1,560,000 (አንድ ሚሊየን አምስት መቶ ስልሳ ሺህ ብር) እንዲተላለፍ በማድረግ፣ 4ኛ ተከሳሽም ገቢ የተደረገለትን ገንዘብ በማስተላለፍ በመንግስት ሰራተኛ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በሚፈፀም የሙስና ወንጀል ልዩ ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት በሀላፊነት አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ተከሰዋል። (የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት፣ ዲሴምበር 11, 2023 እ.ኤ.አ)።*

2. *X የተባለው ተከሳሽ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፒኮክ መናፈሻ ቅርንጫፍ ተቀዳሚ ባንኪንግ ቢዝነስ መኮንን ሆኖ በሚሰራበት ጊዜ የስራ ሃላፊነቱን አለአግባብ በመገልገል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ የፒኮክ መናፈሻ ቅርንጫፍ ደንበኛ የሆኑት*

አቶ Y የቁጠባ ሂሳብ ለረዥም ጊዜ ሳይንቀሳቀስ በመቆየቱ የማይንቀሳቀስ ሂሳብ (Inactive) የነበረውን ወደ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ (Active) በመቀየር፣ ደንበኛው ከሂሳቡ ጋር ለሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ያስተሳሰረውን የስልክ ቁጥር ሲስተም ላይ በመቀየር እና በማፅደቅ ከደንበኛው ሂሳብ ላይ በመቀነስ ተከሳሽ በስሙ በተከፈቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሂሳብ ቁጥሮች በአጠቃላይ 2,435,000 የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት በመጠቀም ወይም በማስተላለፍ መውሰዱ ተመልክቷል።

1. ከላይ ከተጠቀሰው አስረጂ ናሙናዎች ምን መረዳት ይቻላል?
2. በአስረጂ ናሙናዎቹ የተፈጸመዉ የሙስና ወንጀል እርስዎ በሚሰሩበት ድርጅት ውስጥ አጋጥሞ ያዉቃል? ካለ በማን? እንዴት?

2.3.4 የፍላጎት ግጭት

የፍላጎት ግጭት የሚከሰተው ግለሰቦች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተፎካካሪ ፍላጎቶች ሲኖራቸው ነው። ለምሳሌ ከባንኮች የብድር አቅርቦት ውስንነት አንጻር፣ ባንኮች ውስጥ የሚሰሩ ሥራ አስፈፃሚ ግለሰቦች የግል ግንኙነትን መሰረት በማድረግ ስምምንት ላይ ባልተደረሰበት ሁኔታ ብድር ወይም ሌላ አገልግሎት እንዲሰጥ ሊያጸድቁ ይችላሉ።

2.3.5 የውስጥ መረጃን አላግባብ መጠቀም

የውስጥ መረጃን አላግባብ መጠቀም ማለት የስራ ሚስጥርን ላልተፈቀደለት ወይም ለማይመለከተው አካል መግለጽ ወይም አሳልፎ መስጠት እንዲሁም ሚስጥራዊ መረጃን ለግል ጥቅም መጠቀም ነው። ለምሳሌ የባንክ ሰራተኞች ስለመጪው የባንካቸውና የሌላ ባንክ ውህደትን ይፋዊ ባልሆነ መረጃ ላይ ተመስርተው አክሲዮኖችን ሊያገበያዩ ይችላሉ።

2.3.6 አዳኝ/አደገኛ ብድር መስጠት

ይህ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመጠን በላይ ከፍተኛ የወለድ መጠኖችን ወይም ክፍያዎችን በማስከፈል ሲሆን ብዙ ጊዜ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን ያነጣጠረ ነዉ። ለምሳሌ MFIs በተበዳሪዎች ላይ የተጋነነ የወለድ ተመኖችን በመጫን ወደ ዕዳ ዑደት እንዲያመሩ ያደርጋሉ። በሌላ በኩል

ለደንበኞች ግልጽና ተገቢ ያልሆኑ ክፍያዎችን መጫን እንዲሁም ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሰብሰብ ወይም እንዲሰበሰብ ማዘዝ እንደሙስና ወንጀል ይቆጠራል፡፡

2.3.7 የውሸት ሪፖርት ማድረግ

አሳሳች ወይም የተሳሳተ መረጃ ለተቆጣጣሪዎች ወይም ለባለድርሻ አካላት መስጠት አንድ የብልሹ አሰራር መገለጫ ነው፡፡ ለምሳሌ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በገንዘብ ረገድ የተጋነኑ የሚመስሉ የይገባኛል ጥያቄዎችን አሳንሰው ሪፖርት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

2.3.8 ቸልተኝነት እና ደካማ የስጋት አስተዳደር

ትክክለኛ የአሰራር ሂደቶችን አለማክበር የገንዘብ ኪሳራ ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ የባንኮች ጥልቅ የክሬዲት ትንተናዎችን/ፍተሻዎችን አለማካሄድ ብልሹ አሰራር እንዲሰፍንና ተቋማት አደጋ ውስጥ እንዲወድቁ በር ሊከፍት ይችላል፡፡

2.3.9 ሥነ ምግባር የጎደላቸው የግብይት ተግባራት

ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያጋንን ወይም አደጋዎችን የሚያቃልል አሳሳች ማስታወቂያ ማሰራጨት እንደ አንድ ሥነ ምግባር የጎደለው ተግባር ይታያል፡፡ ለምሳሌ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ጉልህ የሆኑ ክልከላዎችን ሳይገልጹ ፖሊሲዎችን የሚያስተዋውቁባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡

2.3.10 የግልጽነት ችግር

ስለ አሰራሮች፣ ክፍያዎች እና አደጋዎች ግልጽ መረጃ አለመስጠት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያጋልጣል፡፡ ለምሳሌ MFIs የብድር ውሎችን ሙሉ በሙሉ አለመግለጽ፣ ተበዳሪዎች ግዴታቸውን በተሳሳተ መንገድ እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፡፡

2.3.11 መድሎ

በዘር፣ በፆታ፣ ወይም ሌሎች መገለጫዎችን መሰረት በማድረግ ከብድር ወይም ከኢንሹራንስ አሰራር ጋር በተያያዘ ግለሰቦች ላይ የሚደረግ ኢ-ፍትሃዊ አያያዝ መድልዎ ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ለምሳሌ ሰራተኛው ራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ባለጥቅም ወይም ባለአክሲዮን ሆኖ ሳለ ራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ከሚሰራበት ድርጅት ጋር ተገቢ ያልሆነ የስራ፣ ንግድ፣ ሽያጭ ግንኙነት ሊፈጥር ይችላል። ያለ በቂ ምክንያትም ለተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መነሻነት ብድር ሲሰጥ ወይም ካሳ ሲከፍል እንደ መድልዎ ይቆጠራል።

ሌላው መድሎ የሚንጸባረቅበት ሁኔታ የሰራተኛ ቅጥር ነው። የሰራተኛ ቅጥርን በሚመለከት ህዝባዊ ድርጅቶች ስማቸው በጎ ባልሆነ መንገድ ሲነሳ እንሰማለን። ለሙስናና ብልሹ አሠራር ከሚዳርጉት ሁኔታዎች መካከል ዝምድናን፣ ብሄርን፣ ሀይማኖትን ወይንም ጥቅምን በማስቀደም አቅምና አግባብ ያለው ልምድ የሌላቸውን ሰዎች ሲቀጥሩ፣ እድገት ሲሰጡ እና የተሻለ ጥቅም ያስገኛሉ የሚባሉ ቦታዎች ላይ ሲመድቡ ይስተዋላል።

2.3.12 የጥቅም ግንኙነት መፍጠር

ሌሎችን በማታለል የጋራ ጥቅምን ለማረጋገጥ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚደረጉ ስምምነቶች ናቸዉ። ለምሳሌ ባንኮች የወለድ ተመኖችን ለማስተካከል ወይም የገበያ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ይተባበራሉ። የኢንሹራንስ ድርጅቶች ሰራተኞች ደግሞ ከመድን ተቀባይ ግለሰቦች ወይንም ድርጅቶች ጋር በመመሳጠር ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ ያልሆነ ወይም የተጋነነ ካሳ እንዲከፈል ሊያደርጉ ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከአገልግሎት ብዛት ወይንም ብልሽት ጋር በተያያዘ ንብረትን ጉዳት እንዲደርስበት ወይንም እንዲጠፉ በማድረግ ባለንብረቱ ግለሰብ/ተቋም የካሳ ክፍያ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ በመድን ሰጪ ኩባንያ ሰራተኞች ከሚፈፀሙ ወንጀሎች አንዱ ሆኖ ይነሳል። ሌላው የባንክ ሰራተኞች በህገወጥ መንገድ የተገኘ ወይም ምንጩ ያልታወቀ ንብረት እና ገንዘብ ህጋዊ እንዲሆን ከወንጀለኞች ጋር ባልተገባ ጥቅም በመተሳሰር ብልሹ አሠራርን ሊያሰፍኑ ይችላሉ።

በሌላ በኩል በግዢ ወይም በሽያጭ የማይገባ ጥቅም መቀበል አንዱና ትልቁ የሙስና ወንጀል ነው። የህዝባዊ ድርጅቶች በአጠቃላይ ከፍተኛ የሆነ የንብረት ግዢና ማስወገድ ያካሂዳሉ፤ ስለሆነም

በግዥ ሂደት ላይ ያላግባብ የጥቅም ተጋሪ ለመሆን ከአቅራቢዎችና ገዢዎች/ተጫራቾች ጋር ህገወጥ ስምምነቶችን ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

2.3.13 የህግ ቁጥጥር መሸሽ

ሆን ተብሎ ከህጎች እና ደንቦች ጋር መጣጣምን ማስወገድ ለሙስና ከሚያጋለጡ ብልሹ አሰራሮች አንዱ ነው፡፡ ለምሳሌ የህዝባዊ ድርጅቶች ሰራተኞች ቅጣቶችን ለማስወገድ ደንቦች ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ሲጠቀሙ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

2.3.14 በስልጣን አላግባብ መጠቀም ወይም መነገድ

በህዝባዊ ድርጅቶች ሀላፊዎችና ሰራተኞች ከሚፈፀሙ ህገወጥ ተግባራት መካከል በስልጣን አላግባብ መጠቀም ወይም በስልጣን ወይም በሀላፊነት መነገድ ዋነኛው ነው፡፡ የድርጅቶቹ ሀላፊዎችና ሰራተኞች የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ የተሰጠን ሹመት፣ ስልጣን ወይም ሀላፊነት ያለአገባብ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

አስረጅ ናሙናዎች/Case Studies 8-12

ከዚህ ቀጥሎ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ ኬዞች ቀርበዉላችኋል፤ ኬዞቹን ካነበባችሁ በኋላ ቀጥለዉ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያዩባቸው፡፡

1. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ የነበረ ሰዉ ከንዳኞቹ ጋር በመመሳጠር በየዕለቱ ከሚሰበሰበዉ ገንዘብ ብዛት ያለዉ (በሚሊዮን የሚቆጠር) ገንዘብ በየዕለቱ እያወጣ ለግል ጥቅማቸዉ እያዋሉ ሲመልሱ ከቆዩ በኋላ በስተመጨረሻ ጓደኞቹ ገንዘቡን ላለመመለስ ወስነዉ ይክዱታል፡፡ ከባንክ ወጥቶ የቀረዉ ገንዘብም በጣም ብዙ ስለነበር ስራአስኪያጁ በራሱ አቅም ለመመለስ የማይታሰብ መሆኑ ሲገባዉና ባመናቸዉ ሰዎች የመካዱን ስሜት ተቋቁሞ በህግ ፊት ቁሞ ለመጠየቅ አቅም በማጣቱ እራሱን አጥፍቷል፡፡ (ምንጭ:- Anonymous.)

2. አስራ ሁለት የአንድ ቤተሰብ አባላት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ የማጭበርበር ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ እንደ ዓቃቤ ሕግ ክስ ከሆነ፣ እነ TT በሚል መጠርያ የሚታወቀው መዝገብ ላይ፣ TT የተባለው ግለሰብ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና መስሪያ ቤት አመራር ሆኖ በሚሰራበት ጊዜ ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በጥቅም በመተሳሰር ታሕሳስ 2012 (እ.ኤ.አ)7.9 ሚሊዮን ብር JBC

ኮንስትራክሽንና WD የተባሉ ድርጅቶች አካዉንት ዉስጥ በተጭበረበሩ ሰነዶች አስተላልፈው ለግል ጥቅማቸው አውለዋል።(ምንጭ፡- www.combanketh.et, በገብረእግዚአብሔር፣ መሰረትና ቶማስ፣ 2014 እንደተገለጸዉ)።

3. በቬትናም የመዋቢያ ዕቃዎችን በመሸጥ ወደ ንግዱ የገቡት ትሩኦንግ፣ የኮሚኒስት ፓርቲ በአውሮፓውያኑ 1986 ያደረገውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተከትለዉ መሬት እና ንብረት መግዛት ጀመሩ። በ1990ዎቹም ስመ ጥር የሆኑ ሆቴሎች እና ምግብ ቤቶች ነበሯቸው። በአውሮፓውያኑ 2011 ትሩኦንግ ማይ ላን በሆቺ ሚኒ ከተማ ውስጥ ስመ ጥር የሆኑ ሀብታም ለመሆን በቁ። እንዲሁም የጥሬ ገንዘብ እጥረት አጋጥሟቸዋል የተባሉ ሶስት ትንንሽ ባንኮችንም ወደ ትልቁ ሳይጎን ንግድ ባንክ እንዲያስገቡም ተፈቅዶላቸው ነበር። የቬትናም ህግ ማንኛውም ግለሰብ በየትኛውም ባንክ ውስጥ ከ5 በመቶ በላይ ድርሻ እንዳይኖረው ቢከለክልም እሳቸው ግን በመቶዎች በሚቆጠሩ የሼል ኩባንያዎቻቸው እና ለሳቸው በሚሰሩ ግለሰቦች አማካኝነት በሳይጎን ንግድ ባንክ ከ90 በመቶ በላይ ድርሻ አላቸው ሲሉም አቃብያነ ህጎች ያስረዳሉ። ያንንም ስልጣን በመጠቀም የራሳቸውን ሰዎች የባንኩ ስራ አስኪያጆች አድርጎ በመሾም እና ለሚቆጣጠሯቸው የሼል ኩባንያዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ብድሮችን እንዲያጸድቁ ትዕዛዝ ሰጥተዋል። ባንኩ ከፈጸመው ብድር ውስጥ 93 በመቶው የሳቸው ብድር ነው ተብሏል። እንዲሁም አቃቤ ህግ እንደሚያስረዳው ከአውሮፓውያኑ 2019 ጀምሮ ባሉት ሶስት ዓመታት ውስጥ በአሽከርካሪያቸው አማካኝነት 108 ትሪሊየን የቬትናም ዶንግ ወይም ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ በጥሬ ገንዘብ አውጥተው ምድር ቤታቸው ውስጥ እንዲያከማቹ ትዕዛዝ አስተላልፈዋል። በተጨማሪም ብድራቸው ጥያቄ እንዳይነሳበት እና ምርመራ እንዳይደረግበትም ጉቦ ሰጥተዋል ተብሏል። ከዚህም ውስጥ ለማዕከላዊ ባንክ ዋና ኢንስፔክተር 5 ሚሊዮን ዶላር ጉቦ እንደሰጡም ክሳቸው ያስረዳል።(ምንጭ፡-https://www.bbc.com/amharic/articles/cxx8k45wp2eo)።

4. በሙስና ወንጀል ከ19 ሚሊዮን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በተባሉ ሁለት የባንክ ሠራተኞች ላይ ክስ ተመስርቶ ነበር። የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የድሬድዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከ19 ሚሊዮን ብር በላይ የሙስና ወንጀል እና ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል በፈፀሙ 2 የብርሀን ባንክ አክሰዮን ማኅበር በደሎ ኦዳ ቅርንጫፍ ሠራተኞች ላይ ክስ መስርቶ ነበር። ተከሳሾቹ ክሱ የተመሠረተባቸው በ2007 ዓ.ም የወጣውን የሙስና ወንጀል አዋጅ ቁጥር 881/07 አንቀፅ 31/2/ እና የወንጀል ሕግ 32/1/ (ሀ) ሥር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች

በመተላለፍ በፈፀሙት ወንጀል ነው:: 1ኛ ተከሳሽ በብርሀን ባንክ አክሲዮን ማኅበር በደሎ ኦዳ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በሚሠራበት ወቅት በባንኩ ተጥሎበት የነበረውን እምነት እና አደራ ወደ ጎን በመተው መጋቢት 16 እና ግንቦት 8 ቀን 2015 ዓ.ም በጥቅሉ ከ18 ሚሊዮን ብር በላይ በማጉደል ለግል ጥቅሙ ያዋለ በመሆኑ በፈፀመው ከባድ እምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ተከሷል::ይህው ግለሰብ በሁለተኛ ክስ ባንኩ ለሠራተኞች ብድር ሲሰጥ ተበዳሪው ፎርም ሞልቶ፣ ዋስ አቅርቦ ለተበደረው ብድር የሚመልስበት ጊዜ ተቀምጦለት ለተበደረው ገንዘብ በሰነድ ማረጋገጫ ሰጥቶ መሆን ሲገባው ተከሳሽ ይህንን ባለማድረግ ለቅርንጫፉ 11 ሠራተኞች 1,151,212.00 (አንድ ሚሊዩን አንድ መቶ ሃምሣ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አሥራ ሁለት ብር) ያለምንም የሰነድ ማስረጃ እና ቅድመ ሁኔታ የሰጠ በመሆኑ:: በተጨማሪም የባንኩ የደንበኞች መኮንን ሆኖ ሲያገለግል የነበረው ሁለተኛ ተከሳሽ ከአንደኛ ተከሳሽ ጋር አረጋግጠው መፈራረም ሲገባቸው ይህን ባለማድረግ ከካዝናው የ19,412,920 (አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ አሥራ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ብር) ጉድለት እያለ በጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መዝገብ (cash register book) ላይ ጉድለት እንደሌለ አረጋግጫለሁ በማለት ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን የፈረመ በመሆኑ ሁላቱ ተከሳሾች የሚሰሩበትን ሊጠብቁት እና ሊከላከሉት የሚገባውን ሕዝባዊ ድርጅት ጥቅም በከባዱ የሚጎዳ ተግባር የፈጸሙ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅትን ሥራ በማያመች አኳኋን መምራት የሙስና ወንጀል ተከሰዋል:: (ምንጭ፦የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት፣ 2016 ዓ.ም)::

5. እነ DA በሚል መጠርያ የሚታወቀው መዝገብ ላይ ተጠርጣሪዎች ከፊላቸው የባንክ ሰራተኞች ሌሎቹ ደግሞ የውጭ ሰዎች በመሆን እርስ በርሳቸው በጥቅም በመመሳጠር ታሕሳስ 2016 (እ.ኤ.አ) ፣ 852,000 ዶላር ከኢትዮጵያን ሺፒንግና ሎጂስቲክስ ሰርቪስ ኢንተርፕራይዝስ በሀሰት ወደተከፈተው ወልካ ኃ/የተ/የግ/ማሕበር በተጭበረበሩ ሀሰተኛ ሰነዶች አማካኝነት ማስተላለፋቸው በመግለጽ ዓቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ መመስረቱን ተከትሎ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል:: (ምንጭ፦ ፍትህ ሚኒስቴር 2014)::

1. ከላይ ከተጠቀሱ አስረጂ ናሙናዎች ምን መረዳት ይቻላል?
2. በአስረጂ ናሙናዎቹ ውስጥ የተፈጸሙት የሙስና ወንጀሎች የትኞቹ ናቸው?
3. መሰል የሙስና ወንጀል እርስዎ በሚሰሩበት ድርጅት ውስጥ አጋጥሞ ያዉቃል? ካለ በማን? እንዴት?

የቡድን ዉይይት

ቀጥለዉ የቀረቡ ጥያቄዎችን በቡድን በመሆን በዝርዝር ከተወያያችሁ በኋላ ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. *ከላይ የተገለጹ የሙስና ወንጀሎች ማለትም ጉቦ፣ማጭበርበር፣ምዝበራ፣የፍላጎት ግጭት፣የውስጥ መረጃን አላግባብ መጠቀም፣አዳኝ/አደገኛ ብድር መስጠት፣የውሸት ሪፖርት ማድረግ፣ ሥነ ምግባር የጎደላቸው የግብይት ተግባራት፣ መድሎ፣ የጥቅም ግንኙነት መፍጠር፣ በስልጣን አላግባብ መጠቀም፣ ወዘተ.እርሶ በሚሰሩበት ድርጅትምን ያህል ይከሰታሉ?*
2. *አንድ የህዝባዊ ድርጅት ሀላፊ ወይም ሰራተኛ አንድን ተግባር ከፈጸመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው ቢጠይቅ እንደሙስና ወንጀል ሊቆጠር ይችላል? እንዴት?*
3. *በዚህ ክፍል ያልተካተቱና በዘርፉ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮችን ዘርዝሩ።*

ማጠቃለያ ጥያቄዎች

1. ከሌሎች የመንግስትና የግል ድርጅቶች አንጻር፣ ህዝባዊ ድርጅቶች ምን ያህል ለሙስና ተጋላጭ ናቸው ብለው ያስባሉ?
2. በህዝባዊ ድርጅቶች በይበልጥ ለሙስና የተጋለጡ አሰራሮች የትኞቹ ናቸው?
3. በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በብዛት ከሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራር ወንጀሎች ውስጥ ሶስቱን ይጥቀሱ?
4. እርስዎ በሚሰሩበት ተቋም ውስጥ የሙስናና ብልሹ አሰራር ወንጀሎች ተከስተው ያውቁ እንደሆን ይግለጿቸዉ።

ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስናወንጀል ያላቸዉ ተጋላጭነት በብዙ መልክ ሊገለጽ እንደሚችል ለማየት ተሞክሯል።እንዲሁም በህዝባዊ ድርጅቶች አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ከፍተኛ የሆነ ሙስና እና ብልሹ አሠራር እንደሚስተዋል ለመዳሰስ ተሞክሯል። ሆኖም ግን ሁሉም በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚታዩ የሙስና እና የብልሹ አሰራር ችግሮች በዚህ የስልጠና ሞጁል ውስጥ ተካተዋል ለማለት አያስደፍርም። ነገር ግን የተቋማቱ ደንበኞች ከሚያነሷቸው ቅሬታዎች እንዲሁም ተቋማቱ ካደረጓቸው ጥናቶች በመነሳት ከላይ የተዳሰሱት ችግሮች ዋነኞቹ ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

እነዚህና ሌሎች የተጋላጭነት ሁኔታዎችን መረዳት አለመቻል ወይም ሆን ብሎ ችላ ማለት ተጋላጭነትን መጨመር ብቻ ሳይሆን ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ሙስና እንዲንሰራፋ በማድረግ ተቋማቱ ላይ የሚኖርን እምነት በመሸርሸር የተቋቋሙለትን አላማ እንዳያሳኩና በአጠቃላይ በሀገር እድገት ላይ የሚኖራቸዉን አስተዋጽኦ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል። እነዚህን የተጋላጭነት መንስኤዎች በአንድ ጀምበር ማጥፋት ላይቻል ይችላል፣ ነገር ግን አሰራሮችንና የየዕለት ተግባራትን እንዲሁም ዉሳኔዎች ለሙስና ተጋላጭ መሆናቸዉን ማወቅ አስፈላጊና የመጀመርያ ተግባር መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነዉ። እነዚህን የተጋላጭነት መንስኤዎች፣ እንዲሁም ግልጽ የሆኑ የሙስና ወንጀሎች ለመቆጣጠር ጠንካራ የአስተዳደር ፍላጎትና ቁርጠኝነት፣የሰራተኞች ተነሳሽነት፣ ጠንካራና ውጤታማ የቁጥጥር ማዕቀፎችና ዘዴዎች፣ ጥብቅ የአተገባበር እርምጃዎች፣ እንዲሁም ጠንካራ የስነምግባር ባህል መገንባትንም ይጠይቃል።

ምእራፍ ሶስት

በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች የሚያስከትሉት ጉዳት እና መከላከያ ስልቶች

3.1 መግቢያ

ሙስና ዘርፈ ብዙ ጉዳቶችን በማድረስ አብዛኛውን ህዝብ ለከፋ ድህነት ከመዳረጉም በላይ የሰዉ ልጆችን ህልዉና ጭምር የሚፈታተን አደጋ ነዉ። ሙስና የተፈጥሮ ሚዛንን የሚያቃውስ አልፎ ተርፎም ሰላም፣ ፀጥታና ፍትህን አደጋ ላይ የሚጥል ማህበራዊ ጠንቅ ሲሆን፤ በሀገር ላይ መጠነ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ ጉዳቶችን ያስከትላል።

በሌላ መልኩ ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው። ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው። ታዲያ ይህን ተለዋዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ ብዙ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል። ሙስናን የመከላከል ተግባር የሙስና ወንጀሎች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ ችግሩን ከምንጩ የማድረቅ ተግባር ነው። ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ለታለመለት ዓላማ እንዲዉል ያደርጋል። በተጨማሪም ችግሩ ከተከሰተ በኋላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ወጪ ያስቀራል፤ በተቋማቱም ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል።

በዚህ አግባብ ይህ ምእራፍ በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች በህዝባዊ ድርጅቶች አሰራርና ሁለንተናዊ ሁኔታ፤ ብሎም በሀዝብና ሀገር ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት፤ እንዲሁም ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይዳሰሳል።

3.1.1 የምእራፉ ዓላማ

ይህ ምእራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ሰልጣኞች፤

1. በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀልች ሰራተኞች ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳት ይረዳሉ፤
2. በዚህ ዘርፍ የሚፈጸም ሙስና በድርጅቶቹ ላይ ያለዉን ተጽእኖ ይለያሉ፤
3. በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸሙ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ህዝብና መንግስት፣ በአጠቃላይ ሀገር ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳት ይተነትናሉ፤
4. የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፤
5. በዘርፉ ውስጥ ያሉ የመከላከለያ ስልቶች ይዘረዝራሉ፤
6. የዘርፋቸውን የሙስና መከላከያ ስልቶች ይገመግማሉ፤
7. በዘርፋቸው የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ።

3.1.2 ለምእራፉ የተመደበው ጊዜ

ይህን ምእራፍ ለመሸፈን የተመደበው ጊዜ 5፡00 ሰዓት ነው።

3.1.3 የምእራፉ አቀራረብ

በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች የሚያስከትሉትን ጉዳት፤ እንዲሁም መከላከያ ስልቶችን በተመለከተ አጭር ገለጻ ከተደረገ በኋላ፣ የቡድን ዉይይት/group discussion/፣ አስረጅ ናሙና/Case Study/፣ ታሪክን መናገር/Story telling/ እና ንጽጽር/Analogy/ ዘዴዎችን በመጠቀም ሰልጣኞች የሙስና ወንጀሎችን ዘርፈ ብዙ ጉዳት በጥልቀት እንዲረዱ ይደረጋል።

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ቀጥለዉ ያሉ ጥያቄዎችን በቡድን በመወያየት የደረሳችሁበትን ለሌሎች ተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚፈጸሙ የሙስናወንጀሎች የሚያስከትሉትን ሀገራዊ ጉዳት ይዘርዝሩ።

2. በእርስዎ እና በተቋምዎ ላይስ የሚያስከትሉት ጉዳት ምን ሊሆን ይችላል?

3. የምታውቋቸውን የሙስና መከላከያ ስልቶች ከነጥቅማቸውን ዘርዝሩ።

4. በህዝባዊ ድርጅቶች ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶችን ዘርዝሩ፡፡

5. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ፡፡

6. ሰራተኞች ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

3.2 በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች የሚያስከትሉት ጉዳት

በሁሉም ዘርፎች የሚፈጸም ሙስና በአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ከባቢያዊ ጉዳቶችንና ቀውሶችን ያስከትላል፡፡ ማለትም የግለሰቦችን ህይዎት ያጎሳቁላል፣ የሀገርን ኢኮኖሚና ዴሞክራሲ ያቀጭጫል እናም ድሀ ሀገራት ድሆች እንደሆኑ እንዲቀጥሉ እና ወደ ግጭትና አለመረጋጋት በመጨረሻም ወደ መፍረስ እንዲያመሩ ያደርጋል፡፡

በሌላ በኩል በሙስና ወንጀል ምክንያት ህዝባዊ ድርጅቶች እንደ ተቋም ተፎካካሪነታቸው ሊቀንስና ከገበያ እስከመውጣትም ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ህዝብና የድርጅቶቹ ባለአክሲዮኖች እንዲሁም ደንበኞች በድርጅቶቹ ላይ አመኔታ እንዲያጡ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ ሰራተኞች እርስ በርሳቸዉ እንዳይተማመኑ፣ ሞራላቸው እንዲጎዳ፣ በተገልጋዮቻቸዉና በህዝብ ዘንድ ዕምነት እንዲያጡ፣ ወዘተ. ሲያደርግ፤ እንደ ሀገርም መጠነ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀዉስ ያስከትላል፡፡

በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸም ሙስናና ስነምግባር የጎደለዉ ተግባር ጉዳቱ መጠነ ሰፊና ዘርፈ ብዙ ሲሆን የተወሰኑትን ብቻ ዘርዘር ባለ መልኩ እንደሚከተለዉ እንመለከታለን፡፡

3.2.1 የገንዘብ ኪሳራ

ሙስና ብዙውን ጊዜ በምላሽ/kick back፣ በጉቦ/bribe እና በደካማ የገንዘብ አያያዝ ምክንያት የተጋነነ ወጪን ያስከትላል፡፡ለምሳሌ ሥነ ምግባር የጎደላቸው የብድር አሰጣጥ ተግባሮች ከፍተኛ የዋጋ ተመንን ያስከትላሉ፡፡ ይህም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትን እና ባንኮችን የፋይናንስ አለመረጋጋት አደጋ ሊያስከትልባቸዉ ይችላል፡፡

በፍትህ ሚኒስቴር የወጡ የምርመራ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት በኢትዮጵያ የባንክ ኢንዱስትሪ በአምስት አመታት ውስጥ ብቻ የ1.8 ቢሊየን ብር የማጭበርበር ኪሳራ ደርሷል፡፡ ከ2017 ጀምሮ 370 ቢሊዮን ብር የሚገመት የማጭበርበር ሙከራ በባንኮች ላይ መደረጉን የጥናት ውጤቱ ያሳያል፡፡ አንዳንድ የኢትዮ ቴሌኮም ሰራተኞችም ከባንክና ከኢንሹራንስ ሰራተኞች ጋር በመሆን በማጭበርበር እጃቸው እንዳለበት ይገለጻል፡፡ የሚከተለዉ ሰንሽረዥ በባንኮች የደረሰን የገንዘብ ኪሳራ ለዓብነት ያህል ያሳያል፡፡

ተ/ቁ	የባንኩ ስም	የጉዳዮች ብዛት	የደረሰው ጉዳት		ድምር	በ%
			ፍጸሜ ያገኘ	በሙከራ የቀረ		
1	ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	78	590,984,925.56	370,520,884.55	961,505,810.11	50.7%
2	አቢሲንያ ባንክ	13	328,939,770.65		328,939,770.65	17%
3	ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ	11	161,839,316.92		161,839,316.92	8.5%
4	ወጋገን ባንክ	4	155,515,965.95	152,800	155,668,765.95	8.2%
5	ኦሮሚያ ሕብረት ስራ ባንክ	2	114,055,605.48		114,055,605.48	6%
6	ዓባይ ባንክ	3	29,607,046.2		29,607,046.2	1.5%
7	ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ	4	28,292,401.5		28,292,401.5	1.5%
8	ዳሽን ባንክ	6	28,231,549		28,231,549	1.5%
9	አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ	1	23,000,000		23,000,000	1.2%
10	አዋሽ ባንክ	17	20,278,738.23		20,278,738.23	1%
11	አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ	3	17,150,000		17,150,000	0.9%
12	ብርሃን ባንክ	2	11,640,774.03		11,640,774.03	0.6%
13	ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ	3	7,727,682.3		7,727,682.3	0.4%
14	ኢትዮጵያ ልማት ባንክ	1	4,800,540.00		4,800,540.00	0.3%
15	ደቡብ ግሎባል ባንክ	2	2,551,200		2,551,200	0.1%
16	ሕብረት ባንክ	4	758,500		758,500	0.04%
ድምር		155	1,525,374,015.82	370,673,684.55	1,896,047,700.37	100%

ምንጭ፦ ገብረእግዚአብሔር፣ መሰረትና ቶማስ (2014)

? ከላይ በሰንጠረዥ ከሰፈረዉ መረጃ ምን መረዳት ይቻላል? እርስዎ በሚሰሩበት ድርጅት በሙስና ምክንያት ስለደረሰዉ የገንዘብ ኪሳራ ምን ማለት ይቻላል?

3.2.2. የመልካም ስም መጉደፍና የዕምነት መሸርሸር

የሙስና ቅሌት የተቋማትን ስም ስለሚያጎድፍ አዳዲስ ደንበኞችን ለመሳብ ወይም ነባሮቹን ለማቆየት የሚደረገዉን ጥረት አስቸጋሪ ያደርገዋል። በአጠቃላይ ተቋማት በሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሲጠረጠሩ የህዝብን አመኔታ ያጣሉ ይህም ከደንበኞች ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ያሻክራል፤ ምክንያቱም ደንበኞች የመልካም አስተዳደር እጦት ወይም መጭበርበርን በመፍራት ገንዘባቸውን እንዲያወጡ ያበረታታል፤ ከሌላ ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋርም የሚኖርን ትብብርና የእድገት እድሎችን ይገድባል።

3.2.3. የስራ ጫና

ሙስና ጥብቅ ደንቦችን እና ቁጥጥርን ሊያስከትል ይችላል ይህም የተቋማትን የስራ ጫና ይጨምራል። በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ድርጅቶች በግለሰቦች ላይ የገንዘብ ቅጣት፣ እገዳ ወይም የወንጀል ክስ ሊመሰርቱ ይችላሉ። ይህ ደግሞ የተቋማቱን ጊዜና ሀብት ይሻማል፣ የስራ ጫናም ይጨምራል።

3.2.4 የተንዛዛ ዓሠራርና ዉሳኔ

ሥነ ምግባር የጎደለው ባህሪ አሰራርን በማንዛዛት ውሳኔ አሰጣጥን ሊያንጓትትና ጥራቱንም ሊጎዳ ይችላል፣ ይህም ወደ ዝቅተኛ የስራ አፈጻጸምና ውጤት ያመራል።

3.2.5 የሰራተኞች ሞራል ዉድቀት

ሰራተኞቹ በሙስና በተሞላ አካባቢ ውስጥ ሲሰሩ ምርታማነታቸዉ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ዝቅተኛ ስሜት ወይም የሞራል ዝቅጠት ሊያስከትል ይችላል። ችሎታና ስነምግባር ያላቸው

ባለሙያዎች በሙስና የሚታሰቡ ድርጅቶችን ሊለቁ ስለሚችሉ ድርጅቶቹ ተሰጥኦ እና እውቀት ያላቸውን ሰራተኞች ወደ ማጣት ሊያመሩ ይችላሉ።

3.2.6 ኢፍትሃዊነት እና ማህበራዊ ተጽእኖ

ሙስና የተወሰኑ በተለይ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ከፋይናንሺያል አገልግሎት እንዲገለሉ ያደርጋል፣ ይህም መገለልንና ኢፍትሃዊነትን ያባብሳል። ከሥነ ምግባር ውጭ የሆነ የብድር አሰራር ተበዳሪዎችን በእዳ አዙሪት ውስጥ በማጥመድ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንቅፋት ይሆናል።

3.2.7 ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ/ጉዳት

ሙስና የመዋእለ ነዋይ ፍሰትን እና ፈጠራን ሊያደናቅፍ ስለሚችል አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገትን ይቀንሳል። ይህም ሸማቾች በድርጅቶች ቅልጥፍና ማነስ እና ሙስና ምክንያት አገልግሎቶችን ለማግኘት ሲባል ለከፍተኛ ዋጋ ሊጋፈጡ ይችላሉ።

3.2.8 የልማት ግቦች አለመሳካት

ሙስና የልማት ተነሳሽነትን በማዳከም ድህነትን መቅረፍ እና ማህበረሰብ ልማት ላይ ያተኮሩ ጥረቶችን ሊያደናቅፍ ይችላል። በተጨማሪም በዘላቂ ልማት ግቦች (SDGs) ውስጥ የተዘረዘሩት ሰፊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግቦችን ያደናቅፋል።

3.2.9 ወንጀል እና አለመረጋጋት መስፋፋት

ሙስና የተደራጁ ወንጀሎች የሚበዙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣ ይህም ወደ ብጥብጥ እና አለመረጋጋት ያመራል። የሙስና መስፋፋት ወደ ህዝባዊ አመጽ ሊያመራና የአስተዳደር መዋቅርን ሊያናጋ፣ እንዲሁም ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን ሊያስከትል ይችላል።

የቡድን ዉይይት

ቀጥለዉ የቀረቡ ጥያቄዎችን በቡድን በመሆን በዝርዝር ከተወያያችሁ በኋላ ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. *በዚህ ክፍል ያልተካተቱና በዘርፉ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራር ጉዳቶችን ዘርዝሩ።*
2. *ከላይ ከተገለጹት እንዲሁም ከዘረዘራችኋቸዉ የሙስና ወንጀሎች ጉዳት እርሶ በሚሰሩበት ድርጅት የትኞቹ ጉዳቶች ተስተዉለ□ል?እንዴት?*

3.3 የሙስና መከላከያ ስልቶች

3.3.1 የቁጥጥርና አስተዳደራዊ ማዕቀፎችን ማጠናከር

ጠንካራ ህግ መቅርጽ ሲቻል ከጅምሩ ለብልሹ አሰራርና ሙስና የሚያጋለጡ ክፍተቶችን መዝጋት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ ብልሹ አሰራሮችን የሚወስኑ እና ከባድ ቅጣቶችን የሚወስኑ ጠንካራ የፀረ-ሙስና ህጎችን ማውጣት እና በቁርጠኝነት ማስፈፀም አስፈላጊ ነው። ይሄንም ለማስቻል ገለልተኛ የቁጥጥር አካላት እና ነፃ ክፍሎችን በማቋቋም እና ደንቦችን ማስከበር፣ እንዳይጣሱ መቆጣጠር እና የሙስና ውንጀላዎችን መመርመር ላይ አስቻይ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው ሊሰሩ ይገባል። ውጤታማነታቸውን ለመገምገም እና አስፈላጊውን ማስተካከያ ለማድረግ የፀረ-ሙስና እርምጃዎችን በመደበኛነት መገምገም ያሻል። ከዚሁ ባልተናነሰ ሙስናን በመዋጋት ረገድ ያለውን ሂደት የሚዘረዝሩ አመታዊ ሪፖርቶችን ማሳተም እና ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ ያስፈለጋል። በዚህ ረገድ የድርጅት ሰራተኞች የማይተካ ሚና እንደሚኖራቸው መረዳት አስፈላጊ ነዉ።

3.3.2 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው። ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል። ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል። በተለይ ሰራተኞች ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባር ጉዳይ ላይ

አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

3.3.3 ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

? *ግልጽነትና ተጠያቂነት ስንል ምን ማለት ነው? ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈንስ እንዴት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ያስችላል? በቡድን በመወያየት ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡*

3.3.3.1 ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፤ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡

ድርጅቶች በሴክተሩ የሚሰጠውን አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በአሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈለገው ወቅትና መጠን ሊያገኙ አይችሉም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

3.3.3.2 ተጠያቂነት

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት/በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን ለመወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል።

ባጠቃላይ የአሰራር ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን መፍጠር ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው። ህዝባዊ ድርጅቶች እድገትን ከማረጋገጥ ባለፈ የሂሳብ አየያዛቸዉን፣ የአሰራር ሂዳቶችን፣ ዉሳኔ አሰጣጥን፣ እንዲሁም የግብይት ዝርዝሮችን ለደንበኞቻቸው እና ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ግልጽነትናና ተጠያቂነትን ማስፈን ይኖርባቸዋል። በብድር ሁኔታዎች እና በሌሎች ቁልፍ መለኪያዎች/ጉዳዮች ላይ ለህዝብ የመረጃ ተደራሽነት በመጨመር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች መከላከል ይቻላል።

በዚህ ረገድ ሰራተኞችም የታማኝነትና ግልጽነት ባህልን ለማሳደግ በእለት ከእለት ተግባራቸው ውስጥ የስነምግባር ባህሪን በመላበስ ለሌሎች ምሳሌ/ሞዴል መሆን ይኖርባቸዋል። በስነምግባር ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ምቾት የሚሰማቸው መሆን ይኖርባቸዋል። ሰራተኞች በነሱ ቁጥጥር ስር ባሉ ጉዳዮች ዙርያ አስፈላጊዉን መረጃ መስጠት ይኖርባቸዋል። ይህ ማለት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች እና በፋይናንሺያል ሪፖርቶች ዙርያ ግልጽነትን መፍጠር ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት እምነትን ይፈጥራልር።

3.3.4 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

? *ስነምግባር ስንል ምን ማለት ነው? በህዝባዊ ድርጅቶች የስነምግባር ደንብን ማዘጋጀትስ እንዴት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል ያስችላል? በቡድን በመወያየት ለተሳታፊዎች አቅርቡ።*

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውሰጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

በመሆኑም በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያትና ተግባራት የሚገልጽ የሥነ ምግባር ደንብ ማዘጋጀት እና ማስፈጸም አስፈላጊ ነው፡፡ ሰራተኞች ከስነምግባር ደንቦች በተቃራኒ ቆመው ሲገኙ ደግሞ በድርጅቶች ውስጥ የሚከሰቱ ማናቸውንም የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮች በመፈተሽ አስተማሪ የሆነ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

3.3.5 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፤ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ በመሆኑም ሰራተኞችና ሀላፊዎች ሀብት እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አበይት ተግባር ሆኖ መቀጠል አለበት፡፡ መከታተያ ክፍሎቹ የሀብት ምዝገባ መረጃንም ለማንኛውም መረጃ ጠያቂ እንዲሁም ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ይሄን ሲያከናውኑ በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ያለን የአሠራር ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስፈን ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

3.3.6 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ የተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው።

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል። በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል።

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል።

3.3.7 የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም። ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል። ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፤ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል። ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል።

3.3.8 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቸዉ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል። ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል። ከነዚህም መካከል፡-

- በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- የጥቅም ግጭትን የመከላከከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

በተጨማሪም በድርጅታቸዉ ውስጥ የስነምግባር ደረጃዎችን በማስተዋወቅ ላይ ያተኮሩ የስነምግባር ኮሚቴዎች ወይም የስራ ቡድኖች ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በመሆኑም አመራሩ በውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ለሥነ-ምግባር ቅድሚያ እንዲሰጡ እና ለድርጊታቸውም ተጠያቂ እንዲሆኑ ማበረታታት ያስፈልጋል።

3.3.9 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው። ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል። እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል።

3.3.10 ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው፤ ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው፤ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

አሰራሮችን በቴክኖሎጂ ማገዝ ቢሮክራሲን እና ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። በመሆኑም ህዝባዊ ድርጅቶች የሚገለገሉባቸውን መተግበሪያዎች/applications በየጊዜው ማዘመንና የተቋማቱን ስራዎች ወይም አገልግሎቶች ከሰዉ ንክኪ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ማለትም ለማጭበርበር የሚከብዱ አስተማማኝ እና ግልጽ ብሎክ ቼይን ቴክኖሎጂን መጠቀም ይመከራል። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ሂደቶችን ለማቀላጠፍ እና የደንበኞችን እርካታ ለመጨመር ያስችላሉ። ስለዚህ ሰራተኞችም ራሳቸዉን ከቴክኖሎጂ ጋር በማቀራረብ ተክኖሎጂን መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።

3.3.11 ጠንካራ የውስጥ መቆጣጠሪያ ስርአትን መተግበር

ሌላው ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን የምንከላከልበት መንገድ ኦዲቲንግ/auditing እና የተገዢነት/compliance መርሃ ግብሮች ስራ ላይ በማዋል ነው። ተከታታይነት ያለው የኦዲት ስራ በመስራት እና ለሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ሪፖርቱን በማቅረብ ክፍተቶችን መለየትና የእርምት እርምጃዎችን መውስድ ያስፈልጋል። መደበኛ የኦዲት ጉድለቶችን ለመለየት እና ከሥነ ምግባር ደረጃዎች ጋር መጣጣምን ለማረጋገጥ ይረዳል። ለምሳሌ ያህል ባንኮች የውስጥ ኦዲት ቁጥጥር ስርአትን መዘርጋት እና ይህንን የአሰራር ሂደት በየጊዜው መፈተሽ ይኖርባቸዋል፤ በተጨማሪም የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ አሰጣጥ ስርአት ሂደት በየጊዜዉ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በሚመጡ ኢንስፔክተሮች ኦዲት መደረግ ይኖርባቸዋል።ከዚህ በተጨማሪ ሰራተኞች እና ደንበኞች አጸፋዊ ምላሽ ሳይሰጡ ሥነ ምግባር የጎደለው ባህሪን ሪፖርት እንዲያደርጉ ደህንነቱ የተጠበቀ የጥቆማ ስርአትን መዘርጋትና ጥቆማ የተሰጠባቸውን ሰራተኞች መመርምርና ጥፋተኛ ሆነው

ሲገኙ ደግሞ ተገቢ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ አሰራር ተግባራዊነትም የሰራተኞች ተሳትፎና አስተዋጽዖ (አስፈላጊ መረጃን በመስጠት፣ ሪፖርት በማድረግና በሚዘረጉ አሰራሮች በመመራት) እጅግ ጠቃሚ ነዉ፡፡

3.3.12 መመሪያዎችን/ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን ማክብር

ሰራተኞቹ የተቋሙን የስነምግባር መርሆች፣ የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎችን እና የቁጥጥር መስፈርቶችን ጠንቅቀው ማወቅና ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የድርጅቶችን ፕሮቶኮሎችና የተቀመጡ ሂደቶችን ማወቅና ማክበር ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

3.3.13 በተከታታይ የሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ መሳተፍ

በሥነ-ምግባር መርሆች፣ ተገዢነት/compliance እና በፀረ-ሙስና ዙርያ የሚሰጡ ስልጠናዎችን በሃላፊነትና ታማኝነት መሳተፍ፤ እንዲሁም ለመረጃ ቅርብ በመሆን በሴክተሩ/ኢንዱስትሪዉ በየ እለቱ ከሚፈጠሩና የቁጥጥር ስረዓት ለውጦች ጋር ራስን በማጣጣም ሊፈጠሩ የሚችሉ የስነምግባርና ብልሹ አሰራር ችግሮችን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ድርጅቶች ስለ ቅንነት እና ታማኝነት ተከታታይ ስልጠናዎችን መስጠት ተገቢ ነው፡፡ በሥነ ምግባር አሠራሮች፣ በፀረ-ሙስና ሕጎች እና በታማኝነት አስፈላጊነት ላይ መደበኛ የሥልጠና ክፍለ ጊዜዎችን መመደብና ማካሄድ ከድርጅቶቹ የሚጠበቅ ተግባር ነው፤ ስልጠናዎችን በንቃትና ሀላፊነት መከታትልና መሳተፍ ደግሞ ከሰራተኛዉ የሚጠበቅ ነዉ፡፡

3.3.14 የሰነድና መረጃ አየያዝን ማሸሻል

ትክክለኛ መዝገብ መያዝና ሰነዶችን ባግባቡ ማደራጀት የማጭበርበር ድርጊቶችን ለመከላከል እና ግልጽ የኦዲት አሰራርን ለመዘርጋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

3.3.15 ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊትን ሪፖርት ማድረግ

ሰራተኞች ማንኛውንም አጠራጣሪ ድርጊቶችን ወይም ስነምግባር የጎደላቸው ድርጊቶችን በተቋቋሙ ቻናሎች አማካኝነት መዘገብና ሌሎች ሰራተኞችም እንዲዘግቡ ማበረታታት

ይጠበቅባቸዋል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዉስጥ ቁጥጥርና ምርመራዎች ላይ መተባበርም ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታት እና ለመቅረፍ ይረዳል።

ባጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ውጥኖች ላይ በንቃት በመሳተፍ ሰራተኞች ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የሚቀንሱ እና ተቋማት ላይ እምነትን የሚያጎለብቱ የስነምግባር ባህሎችን ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ሲሆን ይህንኑ እንደሚከተለዉ ባጭሩ ማስቀመጥ ይቻላል።

1. ለህዝባዊ ድርጅቶች የሚሰሩ ሰራተኞች ከሁሉም አስቀድሞ ለሚሰሩበት ተቋም ህጎች፣ ደንቦች፣ እና መመሪያዎች ራሳቸውን ማስገዛት ይኖርባቸዋል።
2. ማንኛውም በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ግንዛቤ በሚፈጥሩ ስልጠናዎች በመሳተፍ ራሱን በሙስና ምንነት፣ መንስኤዎቹ፣ አይነቶቹ እና መከላከያ መንገዶቹ ዙሪያ በቂ እውቀት ማግኘትና ከማጭበርበር እና ከሙስና ጋር በተያያዘ ዜሮ ታጋሽነት ባህሪን መላበስ አለበት።
3. በተቋማት ወይም ድርጅቶች ውስጥ ማጭበርበር፣ ሙስና ወይም ህገወጥ አሰራር ሲከሰት በቅርበት መከታተልና ማሳወቅ/ሪፖርት ማድረግ የሁሉም ሰራተኞች ሃላፊነት ነው። እያንዳንዱ ሰራተኛ የሙስና ወይም ብልሹ አሰራር ድርጊቶች ሲስተዋሉ ማስረጃዎችን ማሰባሰብና በቅን ልቦና የማሳወቅ ግዴታ አለበት።
4. ማንኛውም ሰራተኛ የሙስና ወንጀል ፈጽሞ በተገኘ ሰራተኛ ወይም ደንበኛ ላይ ለሚወሰድ እርምጃ ወንጀልን የመከላከል ግዴታውን ሊወጣ ይገባል።
5. ሌላው ሰራተኞች ወደ ሙስና ወይም ህገወጥ አሰራር እንዲገቡ ከሚገፋፏቸው ባልደረቦቻቸው፣ ደንበኞቻቸው እና ግለሰቦች ራሳቸውን ማራቅ ይኖርባቸዋል። የሙስና ወንጀል ላይ መሳተፍ እንደ ጀብድ እየተቆጠረ በመጣበት ሁኔታ ራስን ከእነዚህ አካላት አለማራቅ ተጋላጭነትን ሊጨምር ይችላል።
6. ሰራተኞች ሀብታቸውን በማስመዝገብ ለሌሎች ባልደረቦቻቸው አርአያ መሆን አለባቸው። በግል ጥረት ያገኙት ሀብት ወይም ንብረት ቢኖርም እንኳን ደንበኞቻቸው፣ ባልደረቦቻቸውና ማህበረሰቡ በተቋሙ አሰራር ላይ እምነቱ እንዳይሸረሸር ያደርጋል።

7. በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ ሰራተኞች ራሳቸውን ጊዜ ከሚፈቅዳቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር ማስተዋወቅና ማላመድ ይኖርባቸዋል፡፡

የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸም ሙስና በሀገር ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዴት ይገልጹታል? ጉዳቱን ከኢኮኖሚ፣ ከፖለቲካዊ፣ ከማህበራዊ ግንኙነትና ባህል አንጻር ሊመለከቱት ይችላሉ፡፡
2. የሙስና ወንጀል እርስዎ በሚሰሩበት ድርጅት ላይ ምን ጉዳት አድርሷል?
3. በሚሰሩበት ወይም በቅርበት በሚያውቁት ድርጅት የሚፈጸም ሙስና በእርስዎና በባልደረባዎ ላይ ያስከተለው ጉዳት አለ ብለዉ ያምናሉ? አለ ካሉ እንዴት ይገልጹታል?
4. በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኋቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት፤ እንዲሁም ተግባራዊ ያልታደረጉት የትኞቹ ናቸው? ተግባራዊ ከተደረጉ የተገኘው ለውጥ ምንድን ነው? ተግባራዊ ካልተደረጉስ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል?
5. ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር አስረዱ፡፡
6. በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን በዝርዝር አስረዱ፡፡
7. ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከህዝባዊ ድርጅቶች በተለይ ከእርስዎ ድርጅት ምን ይጠበቃል?
8. እንደሀገር የተጀመረው የጸረ ሙስና ትግል ግቡን እንዲመታ ምን አይነት ጉዳዮች ላይ ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል ይላሉ? የእርስዎስ ሚናና ቁርጠኝነት?

ማጠቃለያ

በህዝባዊ ድርጅቶች የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳት መጠነ ሰፊና ዘርፈብዙ ነው፡፡ ጉዳቱም በሰራተኞች፣ በድርጅቶቹ ብሎም በህዝብና ሀገር ደረጃ ሊተነተን ይገባል፡፡ በተለይ የሀገርን ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና ማህበራዊ መስተጋብር ለማወክ ካለዉ አስተዋጽዎ ባሻገር በብዙ ድካም እና መስወዓትነት የተገነባን ሀገር እስከ ማፍረስ ሊደርስ እንደሚችል መገንዘብ የግድ ይላል፡፡ ችግሩን ለመፍታትም ሁሉን አቀፍና የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ ያካተተ አጠቃላይ አካሄድን እንደሚጠይቅ መረዳት ይገባል፡፡

መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም፡፡ በመሆኑም የተቋማትን ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም የሙስናን ተለዋዋጭ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳት፣ እንዲሁም መከላከያ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል፡፡ እነዚህን ዘዴዎች በመተግበር ድርጅቶች የታማኝነት ባህልን ማሳደግ፣ የህዝብ አመኔታን ማሳደግ እና የበለጠ ፍትሃዊ የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖር አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፡፡ ይሁንና ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችም ይሁን የመከላከያ ስልቶቹ እኚህ ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስናወንጀሎችና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በመለየት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ የሚችሉባቸው በርካታ መንገዶች እንዳሉ መረዳት አስፈላጊ ሲሆን፤ ሙስናን መዋጋት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ቀጣይ ሂደት መሆኑንም መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ማጣቀሻ

ህጎች እና ድንጋጌዎች

የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ዓ. ም. ፣የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር 15 አዲስ አበባ የካቲት 12 ቀን 2013 ዓ.ም

የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 881/2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ፣ ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር 10 አዲስ አበባ መጋቢት 7 ቀን 2015 ዓ.ም.

የተቋማት ሪፖርት

ፍትህ ሚኒስቴር (2014). በባንኮች ላይ የሚፈጸሙ የማጭበርበር ወንጀሎች መንሥኤያቸውና የአፈጻጸም ዘዴያቸውን በመለየት የመፍትሔ ሐሳቦችን ለማቅረብ የተዘጋጀ ጥናት።

የIMF የ2016 ሪፖርት

የዓለም ባንክ የ2017 ሪፖርት

የዓለም ባንክ የ2011 ሪፖርት

ዜና/ዘገባዎች

ቬትናማዊቷ ቢሊየነር 44 ቢሊዮን ዶላር በማጭበርበር የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው፣ 11 ሚያዚያ 2024 ቢቢሲ ዜና አማርኛ፣ https://www.bbc.com/amharic/articles/cxx8k45wp2eo

በፋይናንስ ተቋማት የመልካም አስተዳደር ተግዳሮት የኪራይ ስብሳቢነት መገለጫዎች ግምገማ እና የመፍትሄ አቅጣጫዎች መመሪያ. ጥር 2008 ዓ.ም. የኢትዩጵያ ብሄራዊ ባንክ.

በኢንተርኔት ባንኪንግ ከባንኩ ደንበኛ ላይ ከ1.5 ሚሊዮን ብር በላይ በማጭበርበር የተጠረጠሩት ሦስት የአዋሽ ባንክ ሰራተኞች ክስ ተመሰረተባቸው፣ታህሳስ 11, 2023 እ.ኤ.አ፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲን ኮርፖሬት. https://web.facebook.com/EBCzena

በሙስና ወንጀል ከ19 ሚሊዮን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በተባሉ ሁለት የባንክ ሠራተኞች ላይ ክስ ተመሠረተ. 2016 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን. EBC News: አማርኛ

የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ ሐምሌ 23/2016 ዓ.ም አዲስ አበባ

የፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ. የካቲት 21/2016 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

Fana Broadcasting Corporate፡ May 30, 2022.

Corruption and Money Laundering. Global Witness. Retrieved from https://www.globalwitness.org፡ August 31, 2024

ራስን መገምገሚያ ቼክ ሊስት

ከታች ያለዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ ያሉ ሀሳቦችን በማንበብ ‘አዎ’ ወይም ‘አይ’ ስር ቲክ (✓) በማድረግ ይመልሱ።

ተ.ቁ	ሀሳብ/ጥያቄዬ	አዎ	አይ
1	ሙስናና ሌብነት አንድና ያዉ ናቸው		
2	የሀገራት ሁኔታና የህዝቡ ስልጣኔ ቢለያይም የሙስና ምንጭ፣ መልክና ውጤት ግን ያለ ልዩነት ይንጸባረቃል		
3	ባላደጉ ሀገራት ሙስና መጠነ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ቢኖረዉም ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳቱ ግን እምብዛም ነዉ		
4	ህዝባዊ ድርጅት’ ማለት ማንኛዉም የመንግስት መስሪያ ቤት ማለት ነው		
5	በህዝባዊ ድርጅቶች የሚተገበረዉ የብድር አሰጣጥ፣ ክትትልና አከፋፈል ሂደት ለሙስና ያጋልጣል		
6	የህግ ተገዢነት እና ቁጥጥር ስርዓት፣ የሰነድ/መረጃ አየያዝና አጠቃቀም እና አስተዳደራዊ አሰራሮ ለሙስና ሊያጋልጡ ቢችሉም፣ በህዝባዊ ድርጅቶች ግን ያን ያህል አደሉም		
7	ጉቦ፣ ማጭበርበር፣ ምዝበራ፣ የፍላጎት ግጭትና የውስጥ መረጃ አላግባብ መጠቀም በህዝባዊ ድርጅቶች ከሚፈጸሙ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ተርታ ሊሰለፉ ይችላሉ		
8	ጉቦ ማለት አንድ የህዝብ ድርጅት ሰራተኛ በአደራ በተሰጠው እቃ ወይም ንብረት ያለአገባብ ሲጠቀም ወይም በንብረቱ ሲያዝ ሊሆን ይችላል		
9	በዘር፣ በፆታ፣ ወይም ሌሎች ባህሪያት በብድር ወይም በኢንሹራንስ አሰራር ግለሰቦች ላይ የሚደረግ ኢ-ፍትሃዊ አያያዝ ምዝበራ ተብሎ ሊወሰድ ይችላል		
10	የገንዘብ ኪሳራ፣ የመተማመን መሸርሸር፣ኢፍትሃዊነት እና ማህበራዊ ተጽእኖ፣ የስራ ጫና፣ የአሠራርና ዉሳኔዎች መንጓተትና የሰራተኛ ሞራል ድሽቀት መስና በህዝባዊ ድርጅቶች ሊያደርስ ከሚችለዉ ጉዳት ተርታ ሊሆኑ ይችላሉ		
11	ብህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸሙ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በድርጅቱ ላይ እንጂ በሰራተኞችና ህዝብ ላይ የሚያመጡት የተለየ ጉዳት የለም		
12	የህዝባዊ ድርጅቶች ሰራተኞች ስልጣን እስክሌላቸዉ ድረስ ሙስናን ለመታገል አስተዋጽዎአቸዉ እምብዛም ነዉ		

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION

ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et